# አዲስ ዘመን

እሁድ 82ኛ ዓመት ቁጥር 022 መስከረም 22 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!









ፎቶ፡- ገበቦ ገብሬ

# በድምቀት የተከበረው ኢሬቻ ሆረ-ፊንፊኔ


ፍቃዱ ዴሬሳ


አባ ገዳዎችንና ሃደ ሲንቄዎችን በማስቀደም 'መሬዎ'ን እያዜሙ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ታዳሚዎች ወደ ሆራ(ወንዝ) ከማለዳ አንስተው ወደ ስፍራው አቅተዋል። ከንጋቱ ጀምሮ ታዳሚዎች በደማቅ ሁኔታ የኢሬቻ ሆረ-ፊንፊኔን በዓል አክብረውታል።

አባ ገዳዎችና ሃደ ሲንቄዎች የኢሬቻ መርሀ ግብር ወደሚካሄድበት ሆረ-ፊንፊኔ በማምራት ከዘመን ወደ ዘመን በሰላም ላሸጋገራቸው አምላክ የምስጋና ዜማዎችን በማዜም ወደ ሆራ አቅንተዋል። ወጣቶችም በተለያዩ የባህል አልባሳት በማጌጥ የክብረ በዓሉን ዜማ በማዜም ከዋዜማው ጀምረው በዓሉን አድምቀውታል።

ኢሬቻ የምስጋናና የምልጃ በዓል እንደመሆኑ፣ አባ ገዳዎች ምድር እና ሰማይን ለፈጠረ ፈጣሪ (ዋቃ) ምስጋናቸውን አቅርበዋል። "ዝናብ አትንሳን፣ ሰጥተህ አትንሳን፣ ሰውንም ከብቱንም ሰላም አድርግልን፣ አዝመራውን የሰላም፣ ዘመኑንም የሰላምና የጥጋብ አድርግልን፣ የጎደለውን ሙላልን በሀገራችን ሰላም አውርድ" በማለት ተማፅነዋል።


በድምቀት የተከበረው ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል









አቶ ኢፋባስ አብዱልዋክ

# «ዓላማችን አማራን ማዋረድና ማጥፋት ነው እያሉ ልጆቻችን ፊት ደፈሩን»

## (በትህነግ የሽብር ቡድን ታጣቂዎች ተገደው የተደፈሩ እናቶች)


ሙሉቀን ታደገ


የሽብር ቡድኑ ትህነግ ታጣቂዎች በወረራ ይዘው በቆዩባቸው የአማራ እና አፋር አካባቢዎች ህጻናትንና መነኮሳትን አስገድዶ መድፈር ወንጀል ፈጽመዋል። በዚህም በርካታ ህጻናት እና እናቶች ከአካላዊ እና ስነልቦናዊ ጉዳት ባለፈ ራሳቸውን እስከማጥፋት ደርሰዋል።

የሽብር ቡድኑ የትህነግ ታጣቂዎች የአስገድዶ መድፈር ወንጀል ከፈጸሙባቸው አካባቢዎች መካከል የደባርቅ የገጠር ቀበሌዎች ተጠቃሽ ናቸው። የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት የጋዜጠኞች ቡድንም በአካባቢው በመገኘት በሽብር ቡድኑ የትህነግ ታጣቂዎች አስገድዶ መድፈር ያጋጠማቸውን ሴቶች አነጋግሯል።

በደባርቅ የገጠር አካባቢዎች ሽብር ቡድኑ የትህነግ ታጣቂዎች የአስገድ መደፈር ከተፈጸመባቸው ሴቶች መካከል ለዘገባው ሲባል ስማቸውን የተቀየሩት ወይዘሮ


«ዓላማችን አማራን ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል




ፎቶ፡- አዩብ ተፈሪ

# በኢሬቻ በዓል የተሻለ ገቢ ለማመንጨት እየተሰራ ነው


ዋቅሹም ፍቃዱ


አዲስ አበባ፡- በእሬቻ በዓል አገሪቱ የተሻለ ገቢ እንድታገኝ በትኩረት እየተሰራ መሆኑን የኦሮሚያ ቱሪዝም ኮሚሽን አስታወቀ።

የኦሮሚያ ቱሪዝም ኮሚሽን ኮሙኒኬሽን ዳይሬክተር


በኢሬቻ በዓል ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል


# በደቡብ ክልል በመኸር የምርት ዘመን ከ80 ሚሊዮን ኩንታል በላይ ምርት ይጠበቃል


ገጽ 4








«የወታደር ልጅ ነኝ»

- ዮሀና ረታ





ገጽ 6


ፎቶ፡- ገበቦ ገብሬ


ሃደ ሲንቄ ኡርጌ ሮባ


ፈረጃ ፉንጩ


ቆንጪ ሆለታ


ባጫ መገርሳ


ጃተኒ ቦኔ


ትዕግስት ደኖሌ

# «ኢሬቻ የአብሮነት መገለጫና ኢትዮጵያውያን የማንነጣጠል ሕዝቦች የመሆናችን ማሳያ ነው»

**- የበዓሉ ተሳታፊዎች**

**ፍቃዱ ዴሬሳ**

አዲስ አበባ፡- ኢሬቻ የአብሮነት መገለጫና ኢትዮጵያውያን በባህሎቻችን ልዩነት ምክንያት የማንነጣጠል ህዝቦች የመሆናችን ማሳያ ነው ሲሉ በኢሬቻ ሆረ ፊንፊኔ በዓል ላይ የተገኙ የተለያዩ ብሔርና ብሔረሰቦች ተሳታፊዎች ተናገሩ።

የሆረ-ፊንፊኔ ኢሬቻ በዓል ላይ የጋሞ፣ ወላይታ፣ ሲዳማ፣ ጌዲዮን እንዲሁም ሌሎች የተለያዩ ብሔርና ብሔረሰቦች ተወካዮች ተገኝተዋል።

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ካነጋገራቸው ተሳታፊዎች መካከል የሲዳማ ብሔርን በመወከል በበዓሉ ላይ የተገኙት ወይዘሪት ትዕግስት ደኖሌ የኦሮሞ ህዝብ በኢሬቻ በዓል ላይ ለመላው የሰው ልጅ ሰላምና ደህንነትን ፈጣሪውን ዋቃን ይለምናል፤ ያመሰግናል ብለዋል። ይህም የኦሮሞ ህዝብ እንግዳ ተቀባይ መሆኑንና ባህሉም ደማቅ የሆነ ህዝብ መሆኑን እንደሚያመለክት ተናግረዋል።

ኢሬቻ የአብሮነት መገለጫ በመሆኑ የተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎች በበዓሉ በመታደም በአንድነት ማሳለፋቸው ኢትዮጵያውያን አንድነት ያለን ህዝቦች መሆናችንን ያመላክታል። በመሆኑም ይህን የቀደምት አባቶቻችንን አንድነትና ወንድማማችነት እሴት ጠብቀን ለቀጣይ ትውልድ ማስተላለፍ ይጠበቅብናል ብለዋል።

የጋሞና የኦሮሞ ህዝብ ባህል በተወሰነ መልኩ ተመሳሳይነት ያለው እንደሆነ የተናገሩት የጋሞ ተወካይ ቆንጪ ሆለታ በበኩላቸው፤ በየዓመቱ የኢሬቻን በዓል ለማክበር ወደ ሆረ-ፊንፊኔና ሆረ-አርሰዲ የሚመጡ መሆናቸውንና በዓሉን እንደሚያከብሩም ተናግረዋል።

ኢሬቻ የሰላምና የእርቅ በዓል በመሆኑ ሁሉም ማህበረሰብ ለጋራ አንድነት ዘብ መቆም እንዳለበትም ተናግረዋል።

ከወላይታ በበዓሉ ስፍራ የተገኙ ተወካይም በበኩላቸው፤ በዓሉን አብሮ ከማክበር ባለፈ ወንድማማችነታችንና አንድነታችን የሚጠናከርበት በዓል በመሆኑ እንዲህ ባሉ የህዝብ ክብረ በዓሎች በጋራ ማክበር እጅግ አስፈላጊ መሆናቸውን ገልፀዋል።

በሌላ በኩል በዓሉን ከማክበር ባሻገር በእውነተኛ አንድነታችን ላይ በመፅናት ታናናሾችን ታላላቆችን በመስማት በአንድነት እርስ በእርስ መደጋገፍ አለብን በማለት ገልፀዋል።

ከቦረና ዞን በዓሉን የታደመው ወጣት ቦነያ ጃተኒ የኦሮሞ ህዝብ ኢሬቻን በየዓመቱ በማዕከላዊ ደረጃ በአንድ ላይ በመሆን ሲያከብር እርስ በእርሱ የሚገናኝበት ዋነኛ መድረክ በመሆኑ ልዩ ድባብ እንደሚፈጥር ተናግሯል።

በሌላ በኩል ህዝቡ አቃፊ መሆኑን የሚያመላክቱ በርካታ ሁነቶች የሚከናወንበት በመሆኑ የሕዝቡን አንድነት፣ የሀገሪቱን እንዲሁም መላው የሰው ልጆችን በአንድ የሚያስተሳስር መድረክ መሆኑን አመልክተዋል።

በበዓሉ ታዳሚ የሆኑት ሃደ ሲንቄ ኡርጌ ሮባ የኢሬቻ በዓል የጥንት የአባቶቻችንን ባህል ሳይለቅ ለበርካታ ሺህ ዓመታት እየተከበረ መሆኑን አውስተው፤ ለበዓሉ ሰላምን፣ አንድነትን እንዲሁም ምስጋናን የሚያመላክቱ ሲንቄ፣ ጬኮ፣ እርጥብ ሳር እንዲሁም ወተት በመያዝ ወደ ስፍራው መምጣታቸውን ተናግረዋል። ይህም ማኅበረሰቡ ጥላቻን አርቆ ፍቅርን እንዲላበስ፣ ከግጭት ይልቅ ሰላምን እንዲያሰፍን እንዲሁም ከመገፋፋት ይልቅ አንድነትን ለማጠናከር ያለመ መሆኑን ገልፀዋል።

# ተፈጥሮን ይዞ ፈጣሪን ማመስገኛው - ኢሬቻ

**ዳግማዊት ግርማ**



የመስከረም ወር ለኢትዮጵያውያን ከወር ባሻገር ነው። የብርሃን መፈንጠቅ ማሳያ፤ የብሩህ ዘመን ማብሰሪያ ሆኖ ይወሰዳል። ይህ የኢትዮጵያውያን የአስራ ሶስት ወር ጻጋ በተለየ ዓውድ ውስጥ ሆኖ ነው የሚከበረው። ለኢትዮጵያውያንም የአዲስ ዓመት ማስጀመሪያ ወር ነው። ይህ ወር በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎችም ልዩ የዘመን መቁጠሪያ ሆኖ ይከበራል።

ኢትዮጵያ የራሷ ዘመን መስፈሪያ ያላት የአፍሪካውያን የነጻት ቀንዲል እንደመሆኗ ሌላው ዓለም በባርነት ግዞት ውስጥ ሲማቅቅ፤ የአፍሪካ ቀንዴ እንቁ ኢትዮጵያ ግን ነፃነት ወይንም ሞት በሚሉ ልጆቿ የባርነት ቀንበር ሰብራ ወጥታለች። የሌላው ዓለም ታሪክ የሚከተበው በሌሎች ሀገራት ቋንቋ ነበር፤ ኢትዮጵያ ግን ታሪክ ሰርተው ታሪካቸውን በራሳቸው ቋንቋ መፃፍ የሚችሉ ልጆች ያሏት ሀገር ናት።

የባህል ሀብቷሟ ኢትዮጵያ ከሰማንያ በሚልቁ ብሔር ብሔረሰቦች ማንነትና እምነት ጸንታና በክብር ባህልና ወጓን አቻችላ ቀጥላለች። በዚህ ባጋመስነው በአመቱ ቀዳሚው ወርሀ መስከረምም እልፍ ባህል የተንጸባረቀባቸው የዘመን መለወጫ እና ባህላዊ ትውፊት የተንጸባረቀባቸው በዓላት፣ የመስቀል ደመራ፣ ያሆዴ፣ ጊፋታ፣ መስቀላ ዮ እና በኦሮሞ ሕዝብ ዘንድ የሚከበረው የኢሬቻ በዓል የኢትዮጵያዊነት ማንጸባረቂያ በዓላት ናቸው።

በኢሬቻ በዓል ቂም ስፍራውን ያጣል፣ በቀል ማደርያ ቢስ ይሆናል፤ ለጥላቻ ቦታ አይሰጥም፤ ክፋትም ከስር መሰረቱ እንደሚነቀል ይታመናል።

የኦሮሞ አባገዳዎች ህብረት ፀሐፊና የቱለማ አባገዳ ጎበነ ሆላ እንደሚሉት፤ቂምን ይዞ ኢሬቻን ማክበር አይቻልም፤ወንጀል ነው። ቀጣዩን ዓመት በሰላም እና በፍቅር ለመጀመር እርጥብ ሳር ይዞ ከመልካው ዳር በመገኘት ማመስገን ተገቢ ነው። ሳር ለምለም ነው፤ የተስፋ ምልክትም ነው። ውሃም በተመሳሳይ ለሰው ልጅ ከፈጣሪ የተሰጠ ልዩ ፀጋ ነው። እናም በነዚህ የተፈጥሮ ስጦታዎች ፈጣሪን ማመስገን ልመናን ሙሉ ያደርጋል።

ኢሬቻ ፈረንጆቹ Thanks giving day ወይም የምስጋና ቀን ብለው ከሚመሰጋገኑበት ቀናቸው የሚልቅ ከሰው እስከ ፈጣሪ የሚመሰገንበት የኦሮሞ ህዝብ ድንቅ የምስጋና ቀን ሆኖ ይከበራል። በዓሉን ሁሉም ሰው በአንድ ቦታ ተገናኝቶ የሚያከብረው፣ በጋራ የሚመክርበት፣ ስላለፈው እያመሰገነ መጪው ጊዜ መልካም እንዲሆን ፈጣሪውን የሚለምንበት በዓል ነው።

ኢሬቻ ሰንደቅ ነው፤ ሰላምና ይቅርታ ከፍ ተደርጎ የሚውለበለብበት፣ ኢሬቻ ደግ ቃል ነው፤ የፍቅር ዜማ የሚደመጥበት፣ ኢሬቻ መመስጋገኛም ነው፤ መልካም የሆነው ሁሉ የሚሞሸርበት እለት መሆኑም ይነሳል።

በኦሮሞ ሕዝብ ዘንድ ፈጣሪን ዋቃ ሲል ይጠራል፤ በኢሬቻ ባህልም ኦሮሞ ሁሉን በውብ እጆቹ አሳምሮ ለፈጠረ፣ በረሀውን በውሀ ለሞላ፣ የተራበን ላጠገበ፣ ጥም ላጠቃው ህይወትን ለሚያጠጣው ዋቃ/ፈጣሪ/ ምስጋናን የሚቸርበት ቀን ነው።

በኢሬቻ ቀን የክርምቱ ውሃ ሙላት ከመጠያየቅ ያገደው ወዳጅ ዘመድ አምና በቸር ያገናኘን ብሎ ከወንዝ ዳር የተገባባውን ቃልኪዳን በአካል በአይነስጋ በመገናኘት የናፍቆት ጥሙን የሚወጣበት በዓል እንደሆነም ይነገራል።

እንደ አባገዳ ጎበነ ሆላ፤ ኢሬቻ በሁለት መንገዶች ይከበራል፤ አንድም በክረምቱ ወራት ልምላሜን የሰጠኸን አምላክ ተመስገን ሲል ህዝቡ አምላክን የሚያመሰግንበት፤ሁለትም ዓመቱን ሙሉ ችግር አታሳየን የሚልበት የምስጋና እንዲሁም ለመጪው መልካም መሆን ከአምላኩ የሚለማመንበት ቀኑ ነው።

በዓሉ ከሰሜን፣ ከደቡብ፣ ከምዕራብ እና ከምስራቅ ያሉ በተለያዩ የሀገሪቷ ክፍሎች የሚገኙ ህዝቦች ናፍቀው የሚመጡበት በዓል መሆኑንም አባገዳው ይመሰክራሉ።

በኢሬቻ ቀን ሰው በሰውነቱ ብቻ ይከበራል። የት ነህ? ከማን ነህ? እንዴት ነህ? አይባልም፤ በእለተ ኢሬቻ ሃብታም ደሃ፣ ትንሽ ትልቅ፣ ጥቁር ነጭ የለም። ይቅር የማይል ሰው ኢሬቻን ለማክበር ይመጣ ዘንድ የሚፈቅድለት ማንም የለም፤ ክፋትና ክፉ ሀሳብ ከኢሬቻ አከባሪ ወገን እንደሚርቅም ይነገራል።

የዘንድሮው የ2015 ዓ.ም የኢሬቻ በዓል በአዲስ አበባ እና ቢሾፍቱ ባህሉን ወጉንና ስርዓቱን በጠበቀ መልኩ በደመቀ ሁኔታ እየተከበረ ነው።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ከተዛቡ ዘገባዎች በስተጀርባ ያሉ ዓለም አቀፍ ሽልማቶች!

ከፍ ያለ የሙያዊ ስነምግባር ከሚጠይቁ የሙያ መስኮች ዋነኞቹ የመገናኛ ብዙኃን እንደሆኑ ይታመናል።በተለይም ባለንበት ዘመን መረጃ በየትኛውም ዓለም ለሚገኝ ማኅበረሰብም ሆነ ግለሰብ ሊኖረው ከሚችለው የላቀ ፋይዳ አንጻር መገናኛ ብዙሃን ለሙያው ስነ ምግባር ተገዝተው የመገኘታቸው እውነታ ኃላፊነታቸውን በአግባቡ ለመወጣት ወሳኝ የሆነው አቅማቸው ነው።

ዓለም ወደ አንድ መንደርነት እየሄደች ባለችበት፤ የዲጂታል ቴክኖሎጂው የመረጃ ስርጭትን ከመቼውም ጊዜ በተሻለ መልኩ ባቀለለበት፤ ግለሰቦች በእጃቸው በሚገኙ ተንቀሳቃሽ ስልኮች መረጃዎችን በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ ለዓለም ማድረስ በሚችሉበት አለምአቀፋዊ አውድ መገናኛ ብዙኃን በሙያው ስነ ምግባር በመገዛት መረጃዎችን በጥራትና በፍጥነት የማሰራጨታቸው እውነታ ለተልዕኳቸው ውጤታማነት አልፋና ኦሜጋ ጭምር ነው።

በተለይም ባለንበት ዘመን መረጃዎችን የሚያዛንፉ ግለሰባዊ ተቋማዊ እና ሀገራዊ ተጽእኖዎች በስፋት በሚታዩበት፤ የሁሉም ነገር ዋጋ እንደ ሸቀጥ በገንዘብ በሚተመንበት ዓለም አቀፋዊ ሁኔታ ውስጥ መገናኛ ብዙኃን ከፍ ባለ የሙያ ተግዳሮት ውስጥ ለማለፍ መገደዳቸው የማይቀር ነው። ይህን ተግዳሮት አሸንፎ ለመውጣትም ከፍ ያለ የሙያ ስዕብናን መላበስ ያስፈልጋል። ከዚህ ውጪ ሙያዊ ኃላፊነትን ስለ መወጣት ማሰብ የሚቻል አይደለም።

አለም አቀፉ ኅብረተሰብ በተለይም በዓለም አቀፍ ደረጃ "አንቱታ" ካተረፉ የመገናኛ ብዙኃን ተቋማትና ጋዜጠኞች ከሙያ ስነ ምግባር አንፃር የተሻለ አፈጻጸም ይጠበቅባቸዋል። እነዚህ ተቋማትና ጋዜጠኞች የሚያሰሯጯቸው ዘገባዎች ተአማኒነት አሁናዊም ሆነ ቀጣይ ተቀባይነት ችግር ውስጥ እንደሚከተው ይታመናል።

በርግጥ እነዚህ ዓለም አቀፍ የመገናኛ ብዙኃን ተቋማትና ጋዜጠኞች ከቅርብ ዓመታት ወዲህ የቡድኖቹንም ሆነ ባለቤት የሆኑዋቸውን ሀገራት የፖለቲካ ፍላጎት ማስፈጸሚያ እየሆኑ የመምጣታቸው ጉዳይ የአደባባይ ሚስጥር ሆኗል። በዚህም ዓለምን ለብዙ ምስቅልቅል ዳርገዋል። በመገናኛ ብዙሃን የተዛቡ እና ሀሰተኛ መረጃዎች የፈረሱና ለመገንባት ብዙ ዋጋ እየጠየቁ ያሉ ሀገራትን መጥቀስ ለዚህ እውነታ አንዱ ማሳያ ነው።

ከሀገራቱ ህዝቦች በላይ ስለ ሀገራቱ የውስጥ ጉዳይ ተቆርቋሪ /ባለጉዳይ/ ሆነው በመጮህ አለም አቀፉን ህብረተሰብ አሳስተዋል።ጉዳዩ ከማሳሳትም ባለፈ በተሳሳተ መረጃቸው ያልተገቡ እርምጃዎች እንዲወሰዱ በመወትወት የሀገራቱ ሕዝቦች በነሱ የተዛቡ እና ሀሰተኛ መረጃዎች የህይወትን መራራ ፅዋ በግድ እንዲጋቱ አድርገዋል።

ከሁሉም የሚያሳዝነው ደግሞ እነዚህ ዓለም አቀፍ የመገናኛ ብዙኃን ተቋማት እስከ ዛሬ ድረስ ከትናንት ስህተታቸው ከመማር ይልቅ አሁንም በሙያው ስነ ምግባር ዙሪያ አስተማሪና ሰባኪ መሆናቸው፤ ዛሬም የተወሰኑ ቡድኖችና ባለቤት የሆኑዋቸውን ሀገራት የፖለቲካ አጀንዳ ማስፈጸሚያ መሳሪያ ሆነው ሰልፍ የማሳመራቸውና በየአደባባዩ አንዱ ተሸላሚ ሌላው ሸላሚ የመሆናቸው እውነታ ነው።

የእነዚህ መገናኛ ብዙኃን ያልተገባ አካሄድ እንደ ሀገር እኛንም /ኢትዮጵያውያንን /ብዙ ዋጋ እያስከፈለን ይገኛል። ነፃ ያልሆኑ፣ በብዙ ወገንተኝነት የተሞሉና እውነታን መሰረት ያላደረጉ ዘገባዎችን በመስራት ዓለም አቀፉ ኅብረተሰብ በሀገሪቱ እየሆነ ስላለው ነገር ትክክለኛ መረጃ እንዳያገኝ ተግዳሮት ሆነውብናል።

የአሸባሪው ትህነግ እና የሱ ጋላቢ የሆኑ ኃይሎችን ፍላጎት የተከተሉና ለፍላጎቶቻቸው የተገዙ ዘገባዎችን በመስራትና በማሰራጨት፤ ዓለም አቀፉን ኅብረተሰብ ስለሀገሪቱ ያለውን ስዕል ለማበላሸት ረጅም ርቀት ሄደዋል።

የአሸባሪው ቡድን የፕሮፖጋንዳ ማሽነሪ አካል እስኪመስሉ ድረስ በአደባባይ እየተፈጸሙ ያሉ የሽብር ቡድኑ የትህነግን ኢ ሰብአዊ የጭካኔ ድርጊቶችን እንዳላየ ከማየት ጀምሮ የቡድኑን የፈጠራ ዘገባዎችን በማሰራጨት በመንግስት ላይ ጫና ለመፍጠር የሄዱባቸው መንገዶች ለሙያዊ ስነ ምግባር ባዳ አድርጓቸዋል።

እኛ ኢትዮጵያውያን የውስጥ ጉዳያችን ከኛ በላይ ሊያሳስበው የሚችል የለም በሚል አስተሳሰብ ጉዳያችንን በራሳችን አግባብ መፍታት ባንችልና የዚህ ባህል የቆየ ባለቤት ባንሆን ኖሮ በመገናኛ ብዙኃኑ አፍራሽ እንቅስቃሴ ምክንያት እንደ ሀገር ልንከፍል እንችል የነበረው ዋጋ የቱን ያህል አስከፊና መራራ ሊሆን እንደሚችል በተጨባጭ መረዳት የሚከብድ አይደለም።

የእነዚህ የመገናኛ ብዙኃኑ ያልተገባ ተግባር /ስራቸው/ ኢትዮጵያውያንን እያሳዘነና እያስቆጣ ባለበት በዚህ ወቅት የሲ ኤንኤ ዋ ጋዜጠኛ ኒማ አልባጊር ሀገራችንን አስመልክታ ባሰራጨችው የተሳሳተ መረጃ መሸለሚ ሸላሚዎቹ የቱን ያህል ለእውነትና ለሙያ ስነ ምግባር ደንታ ቢስ መሆናቸውን የሚያሳይ ተግባር ነው። ሙያውን በቀጣይም በተመሳሳይ መልኩ የፖለቲካ መሳሪያ አድርጎ ለመጠቀም መሻታቸውን በተጨባጭ ያመላከተና ትዝብት ላይ የሚጥል ነው!

አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

## ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ የኢሬቻ በዓልን ምክንያት በማድረግ ያስተላለፉት መልዕክት

# እንኳን ለኢሬቻ በዓል አደረሳችሁ

**የገዳ ሥርዓት ባለቤት የሆንከው የተከበርከው የኦሮሞ ሕዝብ፤**

**የተከበራችሁ የኢትዮጵያ ሕዝቦች፤**

ከሁሉ አስቀድሜ እንኳን ከክረምቱ ወደ ብርሃናማው መጸው ተሸጋገራችሁ፤ እንኳን ደስ አላችሁ ማለት እፈልጋለሁ።

ሰው ሠራሽ እና ተፈጥሯዊ ችግሮች እንዲሁም ከትንሽ እስከ ትልቅ ጠላቶቻችን የደቀኑብንን አደጋ አሳልፎ ለመጸው ብርሃን ላበቃን ፈጣሪ ምስጋና ይግባው። ኦሮሞ ከገዳ ሥርዓት በወረሰው ዕሴት ክረምት አልፎ መጸው ሲገባ ፈጣሪውን ያመሰግናል።

የክረምቱን ጨለማ አሳልፈህ፣ እህልን አብቅለህ፣ ማሳውን አሳምረህ የመጸውን ንጋት ስላሳየኸን ፈጣሪ ምስጋና ይግባህ ይላል።ርጥብ ሣር ይዞም "መሬሆ" "መሬሆ" እያለ ወደ መልካ በማቅናት የኢሬቻ ሥርዓትን ይከውናል።

ኢሬቻ ክረምት አልፎ መጸው ሲገባ ፈጣሪ የሚመሰገንበት በታላቅ ሥነ ሥርዓት የሚከበር ነው። በድጋሚ የኦሮሞ ሕዝብን፣ በአጠቃላይ የኢትዮጵያ ሕዝብን እንኳን አደረሳችሁ ስል ታላቅ ደስታ ይሰማኛል። ኢሬቻ የሰላም መድረክ ነው።

ለኢሬቻ ወደ መልካ የሚሄዱ ርጥብ ሣር በእጃቸው ይዘው የኢሬቻ ሥርዓትን ከመከወናቸው በፊት ሦስት ጥያቄዎችን መመለስ አለባቸው። የገዳ አባቶች "በመካከላችሁ ሰላም አለ?" "ለፈጣሪስ ሰላማዊ ናችሁ?" "ከተፈጥሮስ ጋር ሰላም ናችሁ?" ብለው ይጠይቃሉ።

ወደ መልካ ለኢሬቻ የሄደው የበዓሉ አክባሪም መልካውን በርጥብ ሣር ከመንካቱ በፊት ሰላም ነው ብሎ ይመልሳል። ከዛም በርጥብ ሣሩ መልካውን ነክቶ "መሬሆ" "መሬሆ" በማለት ፈጣሪውን ያመሰግናል። ለዚህም ኢሬቻን የሚያውቅ ሰው ቂምና በቀልን ትቶ ሰላምን ይሰብካል።

አንድነትና ሰላምን ትብብርና ወንድማማችነትን ያጠናክራል። ከፈጣሪ ላገኘው የከበረ ስጦታ ዕውቅና ይሰጣል። በተፈጥሮ ያለውን መስተጋብርና ትብብር እያደነቀ ለፈጣሪው ምስጋና ያቀርባል። ልምላሜን የፈጠረ አምላክ ከሰው ልጅ ምስጋና ያገኛል። የሰው ልጅ ፈጣሪ የሰጠውን ርጥብ ሣር ይዞ ተፈጥሮን ያደንቃል ፈጣሪን ያመሰግናል።

ኢሬቻን የሚያከብር ከራሱ፣ ከጎረቤቱ፣ ከውስጥና ከውጪ በሀገሩ እና ሩቅ ላለው ሰው ሰላማዊ መሆን አለበት። ለኢሬቻ የሚሄድ ሰው ጥላቻን ትቶ ዕርቅ ማውረድ አለበት። ከኢሬቻ ሲመለስም ቂምና ጥላቻን እንዲሁም ያለፈ ጉዳትን ከማስታወስ ራሱን መቆጠብ አለበት። ኢሬቻን ማክበር በጋራ ምስጋናን ማቅረብ ነው። የተፈጥሮ ሕግ እንዳይስተጓጎል ፈጣሪ በፍጡራን እንዳያዝን ፈጣሪን መለመን ነው።

ስለዚህ ኢሬቻ ዕርቅ ነው። ሰላም ነው ፍቅርና አንድነት ነው። ይህ ደግሞ የገዳ ሥርዓት ባህልና ዕሴት ነው።

ኢሬቻ የንጽሕና መድረክ ነው። ኢሬቻ በሃሳብ መንጻትን ይፈልጋል።

ቂም መያዝና ስም ማጥፋት ከኢሬቻ ዕሴቶች ተቃራኒ ናቸው። ለኢሬቻ የሚሄድ ሰው ይቅር ባይ የሆንከው ፈጣሪ በማለት እጁን ዘርግቶ አምላኩን ይለምናል ያመሰግናል።

በኢሬቻ ሰማይና ምድርን የፈጠረ አምላክ ይመሰገናል።ሐቅን ማዛባት እውነትን መደበቅ ነውር እንደሆነ ይሰብካል። የተፈጥሮና የፍጡራን ሕግ የሚታወቅበት ነው።

የመጸው ወቅት የፈጣሪ የእጅ ሥራ የሚደነቅበት ነው። ከጨለማ ምዕራፍ ወደ ብርሃን ከክረምት ወደ መጸው ከቡቃያ ወደ አዝመራ የምንሸጋገርበትም ነው።

ይህን የፈጣሪ ሥራ የሆነውን የተፈጥሮ ኡደትን "መሬሆ" "መሬሆ" በማለት የሚደነቅበት የኢሬቻ በዓል የብርሃንና የምርቃት ቀን ነው። ኢሬቻ የወንድማማችነት/ እኅትማማችነትና የአንድነት ቀን ነው።

በገዳ ሥርዓት በጋራ ሠርቶ በጋራ መመገብ መተባበርና አብሮ መቆም ለሐቅ መታገልና በችግር ጊዜ መረዳዳት የገዳ ሥርዓት የቀደመ ባህል ነው።

ኢሬቻአንድነትናወንድማማችነት/እኅትማማችነት የሚጠነክርበት ነው። ኅብረት የሚጠነክርበት የፍቅር የወዳጅነት በጋራ የመኖር ምንጭ ሆኖ የሚያገለግል ነው። ይህ ትልቅ ዕሴት የሰው ልጆችን ሁሉ እኩል ማየትና ማክበር በመቅረብ መረዳትን የሚያስተምር ነው። ስለዚህ የበዓሉ አክባሪ ይህን የኢሬቻ ሥርዓትን በማክበር ፈጣሪን ያመሰግናሉ።

ኢሬቻ በዘር በጾታ እና በእድሜ በሃይማኖትና በየትኛውም መሥፈርት ሰውን አይከፋፍልም። ለዚህም ነው ዛሬ ላይ ሁሉም ብሔር ብሔረሰቦች በአንድነት የሚያከብሩት በዓል የሆነው። ለዚህም ነው ከኢትዮጵያውያን አልፎም የውጭ ሀገር ቱሪስቶችን መሳብም የቻለው።

እኛ እንደ ሀገር እና ህዝብ የባህልና ወግ ባለፀጎች ነን፤ የሃይማኖት መቻቻል እና አብሮ መኖርን የሚያጠናክሩ የባህል ሥርዓቶች አሉን። አንዳችን የአንዳችንን ጉድለት ከመፈለግ ይልቅ መደማመጥን ያበረታታል ቂምና ጥላቻን ከመዘመር ሰላምና እውነትን መውደድን ያጠናክራል። የዘፈቀደ እና የስንፍና ኑሮ የኛ አይደለም።

ለሁሉም ነገር ሕግ አለን።በሥርዓትና ወግ ለመኖር እንገደዳለን፤ጀግንነት እንጂ ክህደት እኛን አይገልጸንም ። በታሪክ ውስጥ በአንድነት እንጂ በልዩነት ተከብረን ተፈርተንም ሆነ አሸንፈን አናውቅም። አንድ ሆነን ስንቆም በሁሉም ግንባር ድልን እንደምንጎናጸፍ አይተናል የትኛውንም የሚሸረብብንን ሤራ ማክሸፍ እንደምንችል በተጨባጭ አሳይተናል።

ያለፈው አራት አመት ልምዳችንም ይህንኑ ነው የሚገልጸው። ጠላቶቻችን ወድቀዋል ሲሉን ተነስተን ፈርሰዋል ሲሉን ተገንብተን አይተውናል። አሁንም ብዙ ነጻነታችንን እና ሉዓላዊነታችንን የሚፈታተኑ አሉ፤ ከመንገዳችን ግን ሊያሰናክሉን አይችሉም። ሐቅ አለን፤ እውነት ላይ ቆመን እንታገላለን ፈጣሪም ከኛ ጋር ነው። ለየትኛውም ምድራዊ ኃይል አንንበረከክም። ትልቁ ጠላታችን የሆነውን ድህነት ለማሸነፍ መሥራት ይገባናል።

የሥራ ባህላችንን በማሻሻል በሁሉም የልማት መስኮች ተሠማርተን ለማሸነፍ በቁጭት መትጋት አለብን። ችግርን የመቋቋም አቅማችን በንቃታችን ተደራጅተን አንድነታችንን በጠበቅንና በተጨባጭ ሠርተን ባሳየነው ልክ በችግር በፈተና ጊዜ ካሳለፍነው ልምዳችን ተምረናል።

እንደ ኢሬቻ ያሉ ታላላቅ ክብረ በዓላትን እንደ አንድነታችን ማጠናከሪያ መሣሪያ ይዘን በአጭርና በረዥም ጊዜ የያዝነውን የብልፅግና ጉዟችንን ለማደናቀፍ የተከፈተብንን ዘመቻዎች ሁሉ ጥሰን በማለፍ የያዝነውን ራእይ ለማሳካት በአንድነት እንድንሠራ ጥሪዬን አቀርባለሁ።

የዘንድሮ ኢሬቻ ወደ አዲስ ምዕራፍ የምንሸጋገርበት እና በድል ላይ ድል የምናስመዘግብበት እንዲሆንልን እመኛለሁ።

**ዓመቱ የስኬትና የድል ይሁንልን።**

**ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራና ተከብራ ለዘላለም ትኑር!**

**ፈጣሪ ኢትዮጵያና ሕዝቦቿን ይባርክ!**

**መስከረም 20፣ 2015 ዓ.ም**

# በደቡብ ክልል በመኸር የምርት ዘመን ከ80 ሚሊዮን ኩንታል በላይ ምርት ይጠበቃል

አዲሱ ገረመው



አዲስ አበባ፡- በደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል በዘንድሮው የመኸር ምርት ዘመን ከ80 ሚሊዮን ኩንታል በላይ ምርት ይገኛል ተብሎ እንደሚጠበቅ የክልሉ ግብርና ቢሮ ገለጸ።

በደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል በምክትል ርዕሰ መስተዳድር ማዕረግ የገጠር ክላስተር አስተባባሪና የግብርና ቢሮ ኃላፊ አቶ ኡስማን ሱሩር፤ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳስታወቁት፤ በመኸር ምርት ዘመን የምግብ ዋስትና ለማረጋገጥና ስንዴን ወደ ውጭ ለማላክ በሚያስችል መልኩ ግብርናው ላይ እየተሰራ ነው። በዚህም በክልሉ በመኸር ምርት ዘመን አንድ ነጥብ 2 ሚሊየን ሄክታር መሬት በሰብል የተሸፈነ ሲሆን፤ ከ80 ሚሊየን ኩንታል በላይ ምርትም ይገኛል ተብሎ ይጠበቃል።

ባለፈው ዓመት የተጀመረውን "አንድም ማሳ ጦሙን ማደር የለበትም" የሚለውን ዓላማ ተግባራዊ ለማድረግ የሚመለከተው ሁሉ በግብርናው ልማት ላይ ከቅድመ ዝግጅት ጀምሮ ሲሰራ መቆየቱን አቶ ኡስማን አመልክተው፤ መላው የክልሉ ህብረተሰብ በአንድ መንፈስ ግብርናው ላይ ጠንክሮ እየሰራ እንዳለም ጠቅሰዋል።

በዚህም መነሻ በመኸር በክልሉ አንድ ነጥብ አራት ሚሊዮን ሄክታር መሬት በሰብል በመሸፈን ከ89 ሚሊዮን በላይ ኩንታል ምርት ለማምረት ግብ ተቀምጦ ወደ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ተገብቶ እንደነበር ገልጸዋል።

እንደ አቶ ኡስማን ገለጻ፤ በአብዛኞዎቹ በክልሉ የመኸር ዝናብ በነበረባቸው አካባቢዎች ማሳን በሰብል የመሸፈን ሥራ ከ90 በመቶ በላይ ተሳክቷል። በዚህም ወደ አንድ ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ሄክታር በሰብል ተሸፍኗል። ከዚህም ከ80 ሚሊዮን ኩንታል በላይ ምርት ይገኛል ተብሎ ይጠበቃል። በግብርናው ዘርፍ የተከናወኑ ሥራዎች በምርታማነት ላይ ሰፊ እድል እንዳለም ያመላክታሉ።

በፍራፍሬና አትክልት ልማት ላይ እንዲሁም በስንዴ፣ በጤፍ፣ በበቆሎ፣ በገብስ ባሉ ሰብሎች ላይ ልዩ ትኩረት በመስጠት ጠንካራ ሥራ እየተሰራ እንደሆነ ጠቁመዋል። ከክልል እስከ ቀበሌ ያለው አመራር በተቀናጀ መንገድ ህብረተሰቡን በማነቃቃት የሰብል እንክብካቤ ሥራዎቹ እንዲሳለጡ በማድረግ ላይ እንዳለም አመልክተዋል።

ሀገሪቷ በርካታ ፈተናዎች ውስጥ ብትሆንም ፈተናዎችን እየተሻገረች ወደ ድል የምትሄድበትን ሁሉን አቀፍ ጥረት በማድረግ አመራሩ ተንቀሳቅሶ፤ ህብረተሰቡንና ሙያተኛውን አንቀሳቅሶ፤ የግብርና ልማቱን ከመቼውም ጊዜ በላይ ውጤታማ ለማድረግ የተለየ ጥረት እየተደረገ ይገኛል ብለዋል። ክልሉ የመኸሩ አዝመራ የማሳ እንክብካቤ ላይ እንዳለም ጠቁመዋል።

ስንዴን ከውጭ ከማስገባት ይልቅ ወደ ውጭ መላክ በሚል አቅጣጫ ትላልቅ ስራዎች እየተሰሩ እንዳለ አቶ ኡስማን አስታውቀዋል። የመኸር ዝናብ መቆራረጥ በአንዳንድ የክልሉ አካባቢዎች አጋጥሞ እንደነበር አውስተው፤ ይህንንም በበጋ መስኖ ልማት ለማካካስ ታቅዶ እየተሰራ እንዳለም ገልጸዋል።

ከግብርና ሥራው ጎን ለጎን በሰሜን በኩል ያለው አሸባሪ ሕወሓት ሀገርን ለማፍረስ እያደረገ ያለውን ጥረት የክልሉ ህዝብ እንደ ደጀን በመቆም ለጀግናው መከላከያ ሠራዊቱ አስፈላጊውን ድጋፍ እያደረገ መሆኑንም ተናግረዋል።

# በኢሬቻ በዓል...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

አቶ ኢፋባስ አብዱልዋክ በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የኢሬቻን በዓል ለማክበር ከአገር አልፎ ከሁሉም የዓለም አገራት ብዙ ታዳሚዎች ይመጣሉ። እነዚህ ታዳሚዎች ብዙ ገጸ በረከት ይዘው ስለሚመጡ ለዚያ የሚመጥን ዝግጅት እየተደረገ ነው።

ከዚህ በፊት አሸባሪው ሕወሓት ሆን ብሎ በዓሉን በማወክ ሲሰራ በነበረው ሴራ በዓሉ በብዙዎች ዘንድ እንደሥጋት ሲታይ መቆየቱን ያወሱት ዳይሬክተሩ፤ ነገር ግን ከለውጡ በኋላ በፍጹም ሰላማዊ መንገድ እየተከበረ በመሆኑ የታዳሚዎች ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መምጣቱን ጠቁመዋል።

በተለይ በ2008 ዓ.ም በቢሾፍቱ ኢሬቻ በዓል አከባበር ላይ በንጹሀን ዜጎች ላይ የተፈጸመው ጅምላ ግድያ መላውን ዓለም ያስደነገጠና በበዓሉ ላይ ጥቁር ጠበሳ ያስቀመጠ ክስተት መሆኑንም አውስተዋል።

የጸጥታ ችግር በበዓሉ ድባብ ላይ ሲያሳድር የነበረው አሉታዊ ተጽእኖ እንዳለ ሆኖ ከበዓሉ ጋር ተያይዞ የሚመጣው የቱሪዝም በረከት በባለቤትነት የሚመራውና የሚቆጣጠር ተቋም ባለመኖሩ ከበዓሉ የሚፈለገውን ገቢ ማመንጨት እንዳልተቻለ የጠቆሙት አቶ ኢፋባስ፤ በአንጻሩ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ዘርፉን የሚመራ ኮሚሽን በመቋቋሙ ምንም እንኳ የተገኘውን የገቢ መጠን ለጊዜው መግለጽ ቢያስቸግርም እያደገ መምጣቱ አያጠያይቅም ብለዋል።

በበዓሉ ለሀገር የተሻለ ገቢ ለማስገኘት ኮሚሽኑ ከክብረ በዓሉ ቀን አንድ ሳምንት ቀደም ብሎ የተለያዩ ዝግጅቶች እንደሚደረጉ ያስገነዘቡት ዳይሬክተሩ፣ በዘንድሮ ዓመትም አንድ ሳምንት ቀደም ብሎ በባህላዊ ልብስ ፋሽን ሾዉ፣ በቁንጅና ውድድር፣ በርካታ ሰዎችን ያሳተፈ የእግር ጉዞ ከፒያሳ እስከ መስቀል አደባባይ፣ በቡና ቅምሻ ዝግጅት ምናልባት በዝግጅቱ ላይ በድንቃድንቅ መዝገብ ላይ መመዝገብ የሚችል 10ሺህ ሲኒ የሚይዝ ረከቦት ለእይታ በማቅረብ ጭምር በዓሉ እየተከበረ እንደሚገኝ አመልክተዋል።

ኢሬቻ ከሀገር አልፎ በአውሮፓ፣በአሜሪካና በሌሎች አገራት ሲከበር በሀገር ገጽታ ግንባታ ረገድ የሚጫወተው ሚና እንደ ቀላል የሚታይ አለመሆኑን የጠቀሱት አቶ ኢፋባስ፤ ኢኮኖሚውን በማሳደግ ረገድም ከፍተኛ ሚና እንደሚጫወት ተናግረዋል። ባለፈው ዓመት ዘርፉ በኮሮና ወረርሽኝ ምክንያት የውጭ ሀገር ታዳሚ ቁጥር ቢቀንስም በአሁኑ ጊዜ የውጭ ታዳሚ ቁጥር እየጨመረ መምጣቱንም አብራርተዋል።

በዘንድሮ ኢሬቻ በዓል ላይ ለመታደም 250 የሚሆኑ ኬንያውያን ወደ ኢትዮጵያ መምጣታቸው በዓሉን ልዩ ያደርጋል ያሉት ዳይሬክተሩ፤ በዓሉን ለገጽታ ግንባታና ለቱሪስት መዳረሻ ለማድረግ በሚደረጉ ጥረቶች ሁሉም የበኩሉን ሚና እንዲጫወት ጥሪ አቅርበዋል።

# በድምቀት የተከበረው ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

የኢሬቻ በዓልን ለማክበር የመጡ የሀገር ሽማግሌዎች፣ ወጣቶች እንዲሁም በርካታ ልዩ ልዩ የማኅበረሰብ ክፍሎች ርጥብ የሰርዶ ሳርና አበባ በእጃቸው በመያዝ፣ ሃደ ሲንቄዎች ሲንቄ ወይም ቀጭን በትርና ወተት የያዘ ቅል በመያዝ ከጨለማ ወደ ብርሃን ላሸጋገራቸው አምላክ ምስጋናቸውን አቅርበዋል። "...ፈጣሪያችን ሆይ አንተ ያጸደቅከው ነው አብቦ ፍሬ ያፈራው፤ ለዚህም እናመሰግንሃለን በማለት ወደ ኢሬቻ ስፍራ አምርተው አመስግነዋል፤ ኢሬፈናም አድርገዋል"።

የኢሬቻ ቀንን የተጣሉ ታርቀው፣ ቂማቸውንም ትተው በንጹህ ልቦና ፈጣሪ ንጹህ ወዳደረገው የውሃ አካል በማቅናት እያመሠገኑ መሆናቸውን የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ያነጋገራቸው ተሳታፊዎች ተናግረዋል።

በዓሉ የሰላም፣ የእርቅ እና የአንድነት በዓል መሆኑን ተሳታፊዎቹ ገልጸው፤ በአሁኑ ወቅት በአንዳንድ የሀገሪቱ አካባቢዎች የሚስተዋለውን አለመረጋጋትና ጦርነት በሰላም እንዲፈታ የሁሉንም ጥረት ይጠይቃል ብለዋል።

በአምስቱም የአዲስ አበባ መግቢያ በሮች የገቡ ከተለያዩ የኦሮሚያና ሌሎች የሀገሪቱ ክፍሎች የተገኙ የበዓሉ ታዳሚዎች በተለያዩ ባህላዊ አለባበሶችና ጭፈራዎች ታጅበው በዓሉን በድምቀት አክብረው ውለዋል።

# «ዓላማችን አማራን...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ታሪኳ ይነገር አንደኛዋ ናቸው። ወይዘሮ ታሪኳ የ50 ዓመት አዛውንት ሲሆኑ፤ የሰባት ልጆች እናት ናቸው። የወይዘሮ የታሪኳ የመጨረሻው ልጃቸው ዕድሜ ሶስት ዓመት ሲሆን፤ የመጀመሪያዎቹ ሁለት ተከታታይ ልጆቻቸው እድሜ ደግሞ ጎጆ ለመቀለስ የደረሰ መሆኑን ይናገራሉ።

እንደ ወይዘሮ ታሪኳ ገለጻ፤ ሁሌም ከእንቅልፋቸው ሲነቁ የመጀመሪያ ተግባራቸው ቤተክርስቲያን በመሄድ ጸሎት ማድረስ ነውና ነሃሴ 12 ቀን 2013 ዓ.ም እንደተለመደው ጸሎት ለማድረስ በጠዋት ተነስተው ወደ ቤተክርስቲያን ያመራሉ። ቤተክርስቲያን ጸሎት ላይ እያሉ የሚኖሩበት ቀበሌ በሽብር ቡድኑ መያዙን ይሰማሉ። ጸሎታቸውን አድርሰው እንደጨረሱ ወዲያውኑ ወደቤታቸው ይመለሳሉ። ከሽብር ቡድኑ ጥቃት ራሳቸውን እና ቤተሰባቸውን ለመከላከል በማሰብ ከሰባት ልጆቻቸው ጋር ቤታቸውን ዘግተው ይቀመጣሉ።

የፈሩት ይደርሳል የጠሉት ይወርሳል የሚሉት ወይዘሮ ታሪኳ፤ እንደጠሩ የፈሯቸው የሽብር ቡድኑ ትህነግ ታጣቂዎች ወደ ቤታቸው በመምጣት የቤታቸውን በር አንኳኩ። ነገር ግን እነወይዘሮ ታሪኳ በሩን አልከፍት ስላሉ ይህን ተከትሎ የሽብር ቡድኑ ታጣቂዎች በሩን በሃይል ገንጥለው ወደ ውስጥ ዘለቁ።

በወይዘሮ ታሪኳ ቤት የሚገኝን እህልና ውሃ የሚችሉትን ያህል ከበሉ በኋላ ሲጠግቡ አማራ የሚበላው ማግኘት የለበትም በማለት የተረፋቸውን በቤቱ የሚገኝን አህል በሙሉ አወደሙ። ይህም አልበቃ ብሏቸው ቢላዋ ወደ ወይዘሮ ታሪኳ በማቅረብ አስፈራርተው ለመድፈር ሞከሩ። ወይዘሮ ታሪኳ ለቢላዋው እጅ የሚሰጡ አልሆኑም። በመጨረሻም የሽብር ቡድኑ አባላቱ ጉልበት በመጠቀም ለመናገር በሚዘገንን አኳኋን ወይዘሮ ታሪኳን እየተፈራረቁ ከልጆቻቸው ፊት ደፈሯቸው። ይህንንም ሲያደርጉ "ሁሉንም አማራ እንዲህ ነው የምናደርገው" እያሉና እየዛቱ ነበር።

የወይዘሮ ታሪኳ የመጀመሪያ ሁለት ተከታታይ ወንድ ልጆችም የእናታቸውን መደፈር ሲያዩ የት እንደሄዱ ሳይታወቅ ከቤታቸው ብን ብለው እንደጠፉና እስካሁንም የት እንደሚገኙ እንደማያውቁ ወይዘሮ ታሪኳ ይናገራሉ። የቀሩት ልጆችም እናታቸው ላይ የተፈጸመውን ወንጀል ለመናገር ወደ አያታቸው እና አጎቶቻቸው ወደሚገኙበት ሰፈር አመሩ። የልጆች አያት እና አጎቶችም ከአምስት ሰዓት በኋላ ወይዘሮ ታሪኳ ቤት ደረሱ። ነገር ግን ወይዘሮ ታሪኳ ከቤታቸው ወለል ራሳቸውን ስተው ወድቀው ነበር።

ዘግይተው የደረሱት የወይዘሮ ታሪኳ የቅርብ ቤተሰቦች እጅጉን ተደናግጠው እና ያዩትን ማመን አቅቷቸው ተጠቂዋ ህክምና እንድታገኝ ለማድረግ የባህላዊ አልጋ (ቃሬዛ) ሰርተው ወደ ሃኪም ቤት ለመውሰድ ተነሱ። ይሁን እንጂ የሽብር ቡድኑ የትህነግ ታጣቂዎች በሰሩት ስራ ከማፈር እና ከመሸማቀቅ ይልቅ የአማራ እናት እዚሁ ነው መሞት ያለባት በማለት ወደ ሃኪም ቤት ሄደው ህክምና እንዳያገኙ ከለከሉ።

የወይዘሮ ታሪኳ ቤተሰቦች ሽብር ቡድኑን እግር ጠብቀው ወደ ዋሻ ወስደው ደበቋቸው። ከአራት ቀን ቆይታ በኋላም የሽብር ቡድኑ የሌሉበትን ቦታ በመምረጥ ለሃኪም ቤት አበቋቸው።

በተፈጸመባቸው ጥቃት አሁን ላይ ዓይነ ምድራቸውን እና ሽንታቸውን መቆጣጠር እንደማይችሉ የተናገሩት ወይዘሮ ታሪኳ፤ ካጋጠማቸው አካላዊ ጉዳት በላይ የደረሰባቸው የስነ ልቦና ጉዳት እጅጉን ከፍተኛ እና መሪር መሆኑን ይናገራሉ። በመሆኑም ተወልደው ከአደጉበት እና ባል አግብተው ሰባት ልጆች ካፈሩበት ቀዬ እና ልጆቻቸው ተደብቀው ለመኖር መምረጣቸውን ይናገራሉ።

አሁን ላይ የልጆቻቸው ናፍቆት አላስችል እንዳላቸው የሚናገሩት ወይዘሮ ታሪኳ፤ ከሁሉም በላይ ግን የመጨረሻው የሶስት አመት ልጃቸውን ሁኔታ ሲያስቡት ከሆዳቸው ውስጥ የሆነ አካል ገብቶ አንጀታቸውን የሚስበው ያህል ህመም እንደሚሰማቸው ይናገራሉ። ቢሆንም ግን በደረሰባቸው የስነ ልቦና ጉዳት አሁንም ወደቀያቸው እና ቤተሰቦቻቸው መመለስ እንደማይፈልጉ ይገልጻሉ።

ሌላኛዋ በደባርቅ ወረዳ ገጠራማ አካባቢዎች የምትኖር የነበረችና በሽብር ቡድኑ የትህነግ ታጣቂዎች የአስገድዶ መድፈር ወንጀል የተፈጸመባት የ25 ዓመቷ ወጣት ርስቴ የኋላ (ስሟ የተቀየረ) ነች። ወጣቷ የሁለት ልጆች እናት ስትሆን ልጆቿን ያለ አባት ሻይ እና ጠላ በመሸጥ ታስተዳድር እንደነበር ትገልጻለች።

እንደ ርስቴ ገለጻ፤ ነሃሴ 12 ቀን 2013 ዓ.ም አራት የሽብር ቡድኑ አባላት ከሁለት ልጆቿ ፊት ደፈሯት። የመድፈር ወንጀሉን ከልጆቹ ፊት የፈጸሙት የአማራን ክብር ዝቅ ለማድረግ ታስቦ ነውም ትላለች።

በደረሰባት የአስገድዶ መድፈር አርግዛ እንደነበር የምትናገረው ርስቴ፤ ነገር ግን እንዴት የሰው ልጅ ከማይፈልገው ሰው አርግዞ ሊወልድ ይችላል? ያውም አማራን እንበቀላለን ብሎ ከመጣ ወንጀለኛ በማለት ጽንሱን ማቋረጧን ታስረዳለች።

ጥቃቱ የተፈጸመባት ከሁለት ልጆቿ ፊት ለፊት በመሆኑና የሽብር ቡድኑ ድርጊት ከታላቅ ልጇ አዕምሮ አልጠፋ በማለቱ ታላቋ ልጇ ሌሊት ሌሊት እማዬ መጡብኝ እያለች እንደምትጮህ ትናገራለች።

የተፈጸመባት የአስገድዶ መደፈር ራሷን እስከማጥፋት የሚያደርስ ርምጃ እንድትወስድ አድርጓት እንደነበር የምትናገረው ርስቴ፤ በሰዎች ድጋፍ ራሷን ከማጥፋት ልትመለስ መቻሏን ትጠቁማለች ። ይሁን እንጂ የደረሰባት ስነ ልቦና ህመም እጅጉን ከፍተኛ በመሆኑ ዘመድ አዝማዶቿን እና የትውልድ ሰፈሯን ወደማታይበት አካባቢ ለመሰደድ መገደዷንም ገልጻለች።

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ



በቁምላቸው አበበ ይማም (ሞሼ ዳያን)
fenote1971@gmail.com

ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል።በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

## የእርቅና የአብሮነት ማዕድ ... !?

ዓለም አቀፉ የእርቅ፣ የሰላም፣ የግልግልና የሽምግልና ረቡኒ (መምህር ) ፕሮፌሰር ሕዝቅያስ አሰፋ "የሰላምና ዕርቅ ትርጉምና መንገዶች" በሚለው ማለፊያ መጽሐፋቸው የሰላም የእርቅ አድማሶች በማለት በመጀመሪያ ሰው ከራሱ ጋር ከዚያ ከጎረቤቱ ፤ ከማኅበረሰቡ ጋር በመጨረሻም ከተፈጥሮ ጋር እርቅ ፤ ሰላም ማውረድ እንዳለበት ይተነትናሉ ። ትናንት የተከበረው የኢሬቻ በዓል ሰው በመጀመሪያ ከራሱ ጋር በመቀጠል ከጎረቤቱ ከዚያም ከተፈጥሮ ጋር የሚታረቅበት ማዕድ ነው ።

ኢሬቻ ሰላም ፣ ፍቅር ፣ ይቅርታና አንድነት የሚፈፀምበት በመሆኑ አብሮነትን ስለሚያበረታታ አሰባሳቢ ነው ። ጥልን ቂምን ጥላቻን እያራገፈ መልካም መልካሙን ማለትም ሰላምን ዕርቅን የሚያጠናክር ስለሆነ በውስጠ ታዋቂ ማካበትን ይዟል ። ኢሬቻም ሆነ ዐቢይ መገለጫው የሆነው እርቅ ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲተላለፍ ፣ ሲቀባበል ፣ ሲወራረስ የመጣ በሂደትም እያደገ እየጎለበተ ስለሆነ ማከማቸትን አካቷል ።

የኦሮሞ ባህልና ታሪክ ተመራማሪና ፀሐፊ አቦ ድርቢ ደምሴ ኢሬቻ ማለት ኦሮሞ ለምለም ሳርና አበባ ይዞ ፈጣሪን የሚያመሰግንበት ክዋኔ ሲሆን በሐይቅ ፣ በወንዝ ፣ በምንጭ ወይም በውሃ ዳርና በተራራ ብቻ የተወሰነ ግን አይደለም ይላሉ ። ልጅ ሲወለድ ፣ አዲስ ቤት ሲሠራ ፣ ሙሽራ ሲወጣ ፣ በዘር ወቅትም ፣ ወዘተረፈ ኢሬቻ ይደረጋል በማለት ከማኅበረሰቡ የዕለት ተዕለት ሕይወት ጋር ምን ያህል የተቆራኘ እንደሆነ ያስረዳሉ ። የኦሮሞ ተወላጅ የሆኑት አቦ ሙሉጌታ ደበበ (ፒ ኤች ዲ) በሌላ በኩል ኢሬቻ የገዳ ሥርዓት አንዱ አንጓ ነው ይላሉ ። በማሳያነት ከሚጠቀሱት ዓበይት ምክንያቶች ቀዳሚው የሥርዓቱ ክዋኔ በቃሉና በአባ መልካ አጋፋሪነት መመራቱ ነው በማለት በዋቢነት ይጠቅሳሉ።

ኢሬቻ በኦሮሞ ማኅበረሰብ ዘንድ በዓመት ሁለት ጊዜ እንደሚከወንና የመጀመሪያው በበልግ በተራራ ላይ አምላክን የሚያመሰግንበትና ዝናብ የሚለማመንበት ሲሆን ቱሉ ኢሬቻ ይሰኛል ። አቦ ድርቢ ቱሉ ኢሬቻ መሬት አፏን ከፍታ የበልግ ዝናብን የምትጠብቅበት ወቅት ስለሆነ ፈጣሪን ዝናብ የሚለማመኑበት ጊዜ መሆኑን ይገልጻሉ ። ባለፈው ሳምንት ለምለም ሳርና አበባ ተይዞ በሐይቅ ፣ በወንዝ ፣ በምንጭ ዳር የተከበረው የምስጋና በዓል ደግሞ መልካ ኢሬቻ በመባል እንደሚታወቅ አቦ ሙሉጌታ ያብራራሉ ።

ፈጣሪ ዝናብ ስለሰጠ ከክረምት ወደ ብራ ስለ አሸጋገረ የሚመሰገንበት እንዲሁም አዝመራው ደርሶ ተሰብስቦ ወደ ጎተራ እንዲገባ የሚለመንበት መሆኑን አክለው ይገልጻሉ ። በፕሮፌሰር የሰላም አድማስ እይታ መሠረት ኢሬቻ ሦስቱንም የሰላም አለባውያን በአንድነት የያዘ የእርቅ ፣ የሰላም ገበታ ነው ማለት ይቻላል። ሦስቱን የሰላም አድማሶች ከኢሬቻ እሴቶች አንጻር አንድ በአንድ እናመሳክር ፡-

### 1ኛ. ከራስ ጋር ሰላም ፤

ዓለም አቀፍ አሸማጋይ እና የሰላም አባት ፕሮፌሰር ሕዝቅያስ ከፍ ብሎ በጠቀስሁት መጽሐፋቸው ገፅ – 102 ላይ"ውስጣዊና መንፈሳዊ ሰላም ከራስ ጋር ሰላም ማውረድ ፣ መታረቅ ነው ። ከፈጣሪ ጋር ሰላም ከማውረድ ጋር ትስስር አለው ። ውስጣዊ ሰላም ከሌሎች ጋር ለሚመሠረት ሰላም ወሳኝ ነው ። ውስጣዊ ሰላም ያለው ሰው ምን ያህል ከሌሎች ጋር በሰላም እንደሚኖር እና ሰላም እንደሚያካፍል ይታወቃል ። ውስጣዊ ሰላም ያላቸው ሰዎች አስታራቂና ሰላም ገንቢም ናቸው ። ሰላማቸው ወደሌሎች ይፈሳል ። ከራሱ ጋር የታረቀና ውስጣዊ ሰላም ያለው ሰው የሕይወትን መስተጋብር የተገነዘበ ስለሆነ ከማኅበረሰቡና ከተፈጥሮ ጋርም ሰላምና እርቅን ያወረደ ነው ። ከራስ ጋር የሚፈጠር ሰላም ለሰላም አድማሶች መነሻም ውጤትም ነው ። ..."

ኢሬቻ ከመደረጉ በፊት ከራሱ ጋርም ሆነ ከሌሎች ጋር የተቀያየመ የተጋጨ ካለ እንዲወጣ ሽማግሌዎች በኦሮሚኛ "እውነትን ከአምላክ ፆታን ከምድር መደበቅ አይቻልም ። በውሻም ሆነ በልጅ ምክንያት የተጋጨ ካለ ከፈጣሪ ጋር እንዳያቀያይመን ይውጣ" በማለት እንደሚያግባቡ ይህን ሳያደርጉ ቢቀሩ ደግሞ በማኅበረሰቡ ዘንድ እንደሚያስወቅሳቸው አቦ ድርቢ ያስረዳሉ። የሀገር ሽማግሌዎች ቢያንስ በመጋቢትና በመስከረም በዓመት ሁለት ጊዜ እርቅ የማውረድ የመሸምገል አጋጣሚ እንዳላቸው ይገልጻሉ ። ሰሞኑን የተከበረው መልካ ኢሬቻም ሆነ በወርሐ መጋቢት የሚከበረው ቱሉ ኢሬቻ ላይ ተሳታፊ ለመሆን ከራስ ጋር መታረቅ ሰላም ማውረድ ማኅበራዊ ቅድመ ሁኔታ እንደሆነና በዓሉ ቤትን ራስን በእርቅ የማፅዳት ፤ የጥል ግድግዳን የማፍረስና ፋይል ዘግቶ ወደ አዲስ ምዕራፍ የመሻገሪያ ድልድይ መሆኑን አቦ ሙሉጌታ አክለው ያብራራሉ።

### 2ኛ. ማኅበራዊ ሰላም፤

ፕሮፌሰር ሕዝቅያስ ስለ ሁለተኛው የሰላም አድማስ ገጽ – 103 ላይ"ማኅበራዊ ሰላም ከራስ ጋርና ከተፈጥሮ ጋር ከሚደረግ ሰላም ጋር ጥብቅ ትስስር አለው ። ይህ ማለት ግን ማኅበራዊ ሰላም ከሌለ ውስጣዊ ሰላም አይኖርም ወደሚል መደምደሚያ አያደርስም ። ሆኖም ብጥብጥና ሁከት ባለበት ውስጣዊ ሰላምን ማስፈንንም ሆነ ማስቀጠልን ፈታኝ አያደርገውም ማለት አይደለም። ሌላው ማኅበራዊ ሰላም ከተፈጥሮ ጋር ከሚደረገው ሰላም ጋር ጥብቅ ትስስር ያለው መሆኑን መገንዘብ ነው ። ግጭትና ጦርነት በተደጋጋሚ የተካሄደባቸው አካባቢዎች የሚገኝ የተፈጥሮ ሀብት ስለሚጎዳ ደኑም ስለሚጨፈጨፍ አካባቢው ይራቆታል። በዚህም ሥነ ምሕዳሩ ስለሚዛባ የከባቢ አየር ለውጥን ያስከትላል ። ለዚህ ነው የማኅበራዊ ሰላም መኖር ለፍጥረትና ለአካባቢ ጥበቃ ዋስትና ተደርጎ የሚወሰደው።"ፕሮፌሰር እንደሚሉት ከራስ ጋር የሚፈጠር ውስጣዊ ሰላም ከጎረቤትና ከማኅበረሰብ ጋር የሚደረግ እርቅ መሠረት ነው። በኢ-ሬቻ ለመታደም ከራስ ጋር መታረቅ ማኅበራዊ ቅድመ ሁኔታ ነው ። ከራሱ ጋር ሰላም ያለው ደግሞ ከጎረቤቱ ጋር የመጋጨት አጋጣሚው ዝቅተኛ ነው ።

ሆኖም ከጎረቤቱ ጋር ወይም ከሌላ ሰው ጋር ግጭት ቢፈጠር የሀገር ሽማግሌዎች በቱሉ ወይም በመልካ ኢሬቻ የማስታረቅ መልካም አጋጣሚም ኃላፊነትም ስላለባቸው ማህበራዊ ሰላምን ከመታወክ ይታደጉታል። ለዚህ ነው የሥነ ማኅበረሰብ አጥኚዎች መጀመሪያ ከራስ በመቀጠል ከጎረቤት ጋር የሚፈጠር ሰላም ከተፈጥሮ ጋር ለሚደረስ ሰላም መደላድል እንደሆነ የሚያስረዱት። ታላቁ መጽሐፍስ"እኔ እንደ ወደድኋችሁ እርስ በርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ ትእዛዜ ይህች ናት።"አይደል የሚለው!?

### 3ኛ. የተፈጥሮ ሰላም፤

ፕሮፌሰር በገፅ – 104 ላይ"የተፈጥሮ ሰላም ከማኅበራዊ እና ከውስጣዊ ሰላም ጋር ጥብቅ ትስስር አለው ። ከተፈጥሮ ጋር ሰላም ፣ እርቅ ማውረድ አካላችን ከታነፀበት ምድር ጋርም መታረቅ ነው ። ከተፈጥሮ ፣ ከዩኒቨርስ ሥርዓትና ኃይል ጋር መንሰላሰል የውስጣዊ ሰላም ምንጭ ነው። ...የተፈጥሮ ፍቅርና እንክብካቤ ለማኅበራዊ ሰላም መስፈን የማይተካ ሚና እንዳለው የተለያዩ ጥናቶች ያረጋግጣሉ። ..." ኢሬቻ ከሁለቱ የሰላም አድማሶች ይልቅ ከተፈጥሮ ጋር ለሚደረግ እርቅ ያደላል ቢባል ማጋነን አይሆንም። በቱሉ ኢሬቻ ፈጣሪውን ለበልግ እርሻ ፣ ለከብቶች ግጦሽና ለውሃ ዝናብ የሚለምንበት መሆኑ መልካ ኢሬቻው ደግሞ ፈጣሪው ዝናብ ስለሰጠው ፣ ከክረምት ወደ ብራ ስላሸጋገረው የሚያመሰግንበት በሌላ በኩል ያልተሰበሰበውን እህል በአደራ የሚሰጥበት የአምላክን ጥበቃ የሚለማመንበት መሆኑ በተለይ ለምለም ሳርና አበባ ይዞ ውሃ ዳር ፈጣሪ የሚመሰገንበት መሆኑ ከተፈጥሮ ጋር በእጅጉ የተቆራኘ መሆኑን ያሳያል ። ይሁንና ኢሬቻ ደረጃው ፣ ስፋቱ ፣ ጥልቀቱ በየሰላም አድማሱ የተለያየ ቢሆንም ሰው ከራሱ ፣ ከጎረቤቱ በመጨረሻም ከተፈጥሮ ጋር በአንድ የእርቅ ፣ የሰላም፣ የመቀባበል ፣ ወዘተ . ማዕድ ቀርቦ የሚቋደስበት ስለመሆኑ አያጠያይቅም ።

ፕሮፌሰር ሕዝቅያስ"...በተለያዩ ማኅበረሰቦች ሀገር ግንባታ Nation Building በመሀላቸው ያለውን ልዩነት አጥብቦ ግድግዳዎችን አፍርሶ የጋራ ማንነት መገንባት ነው ። ..." ይላሉ። የሀገር በቀል እውቀቶችና የባህል ተመራማሪው አቶ አብዱልፈታህ አብደላ ይሄን የፕሮፌሰር ሀሳብ ይጋራሉ። በዓሉ በአዲስ አበባ ሌሎችን የማኅበረሰብ ክፍሎች ባሳተፈ አግባብ መከበሩ ለሀገረ ግንባታ መሠረት ጥሏል ማለት ይቻላል ሲሉ ዘላቂ ፋይዳውን ያመላክታሉ ። የጋራ የሆኑ እሴቶችን ባህሎችን እያጎለበትን እያሳደገን በሄድን ቁጥር መተዋወቅ ፤ መከባበር ፤ መቀባበል ስለሚጨምር እኔነት በእኛነት እየተተካ ስለሚሄድ ለሀገርም ሆነ ለሀገር መንግሥት ግንባታ እርሾ እንደሚሆን ተመራማሪው ያስረዳሉ ።

ዛሬ ከምንገኝበት መንታ መንገድ ላይ የደረስነው ባህሎቻችንን እሴቶቻችንን ለሀገር መንግሥትም ሆነ ለሀገር ግንባታ ባለማዋላችን ነው ሲሉ አቶ አብዱልፈታህ ይሞግታሉ ። አቦ ሙሉጌታ በበኩላቸው እንደ ዓድዋ ያሉ የድል በዓሎቻችን ፣ ኢሬቻ ፣ ሻደይ ፣ አሸንዳ፣ ፍቼ ጨምበላላ ፣ ጊፋታ ፣ ወዘተረፈ አንድ የሚያደርጉን ባህሎች በበዙ ቁጥር ኢትዮጵያዊነታችን ይጠናከራል። ከተገኘንበት ብሔር ይልቅ ኢትዮጵያዊነታችን እየገዘፈ ይሄዳል። እየተዋሀድን ፣ እየተቀባበልን፣ እየተከባበርን በሄድን ቁጥር እየተዋደድን እንሄዳለን አንድነታችንም በዚያው ልክ ይጎለብታል ሲሉ ይጠቁማሉ ።

### ስከርሞ...!?

ፈጣሪ የከርሞ "ሕዝብ" ካለን መስቀልንም ሆነ ኢ-ሬቻም ወይም ጊፋታ ፣ መስቀላዮም ሆነ ፍቼ ጨምበላላ አሸንዳ ሻደይም ሆነ ሶለል ፣ ወዘተረፈ ሲከበሩ በተቻለ መጠን ከፖለቲካዊ አንድምታ ጋር ላለማቆራኘት የተደረገው ጥረት ከርሞም ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል። በሽግግር ፣ በመሠራት ላይ እንዳለ ሀገርና ሕዝብ በተወጠረች ፖለቲካዊ ገመድ በጥበብ በማስተዋል መጓዝ ግድ ይለናል። እሴቶቻችን ባህሎቻችን በራሳቸው ሙሉ፣ ጮኸው የሚናገሩ ፣ ከሩቅ እንደ ቀስተ ዳመና ደምቀው የሚታዩ ስለሆኑ ምንም ዓይነት ማጋጌጫ አያሻቸውም ። ቱባ መሆናቸው በራሱ ሙሉኡ አድርጓቸዋልና። አቶ አብዱልፈታህ ኢሬቻ ከበርካታ ዓመታት በኋላ ወደ አዲስ አበባ ይዞልን የሚመለሰው ምስጋናን፣ ይቅርታን ፣ ሰላምንና አንድነትን እንጂ ሌላ አጀንዳን ሊሆን አይገባም ይላሉ። ሌላው ኢትዮጵያዊ ደግሞ ኢሬቻ ወደ ጋራ መድረክ ወደ አንድነት ሲመጣ እንኳን ደህና መጣህ ብሎ ሊቀበለው ይገባል በማለት አበክረው አሳስበዋል ።

ሆኖም የክልል ሰንደቅ ዓላማ እና የፓርቲ ዓርማ በማንገብ ፖለቲካዊ ቡልኮ መደረቡ ተገቢ አለመሆኑ ከዓመት ዓመት ግንዛቤ ያገኘ ይመስላል ። ይህ ከኢሬቻም ሆነ ከሌሎች በዓላት እሴቶች ጋር የሚጣረስ ከመሆኑ ባሻገር አቃፊነቱ ላይ ጥያቄ ፣ ብዥታ ፣ ግርታ ሊያስነሳ ይችላል ። ከባህላዊ ፣ እሴታዊ አንድምታው ይልቅ ፖለቲካዊ ቱማታው ላይ ጊዜያዊ ነጥብ ለማስመዝገብ የሚደረግ መሽሎክሎክ ዘንድሮ ደብዘዝ ማለቱ ይበል የሚያሰኝ ነው ። ከሀገራዊ ፣ ከቀጣናዊ ፣ ከአህጉራዊና ከዓለም አቀፋዊ ስትራቴጂና ሕልማችን አንጻር አሉታዊ ተፅዕኖ እንዳይኖረው ሀይማኖትንና በዓላትን ለአማኙና ለተከታዩ መተው ሊበረታታ ይገባል ። በነገራችን ላይ ሀይማኖትንና ባህልን ከፖለቲካ ጋር የማጣቀስ አባዜያችን ትናንት የተጀመረ አይደለም ። የዋለ ያደረ አባዜ እንጂ። ይህ ጥርሻ በዜጎች መካከል መጠራጠርን፣ ልዩነትን የሚያነብር ስለሆነ ሰከን ብሎ ማሰብ ይገባል። ለብሽሽቅ፣ ለእልህ ፖለቲካ በር እንዳይከፍት ጥንቃቄ ማድረግም ያስፈልጋል።ከሁሉም በላይ እንደኛ በሽግግር ላይ ላለ እና ጠንካራ ዴሞክራሲያዊ ተቋማትን ላልገነባች ሀገርና ሕዝብ ፖለቲካዊ ትክክለኝነት Political Correctness የልብ ትርታዋ ሊሆን በተገባ። ሆኖም በገዥው ፓርቲም ሆነ በተፎካካሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች የአፍ ወለምታ፣ ግራ ቀኙን ካለማመዛዘን ፣ የመራጭን constituency ቀልብ ለመግዛት ፣ "የአንቂን" Activist ቡራኬ ለማግኘት የሚፈፀሙ ፖለቲካዊ ስህተቶች ሀገርንም ሆነ ለውጡን ያልተገባ ዋጋ ሲያስከፍሉት ኑረዋል ። አንዳንድ ፖለቲከኞቻችን ለጭብጨባ ተሚጋች ነን ባዮች ለሰብስክራይብና ለላይክ ሲሉ በስሜት ከመጋለብ ዛሬም ሳይረፍድ ራሳቸውን በልጓም ፣ በልባብ ሊገቱ ይገባል ። ወደ መነጋገሪያው ቀርቦ አንደበትን ከመክፈት በፊት ሁለት ሦስቴ ማሰብና ከስሜታዊነት መታቀብ ያስፈልጋል ። ገና ብዙ ያልተሻገርናቸው ሸለቆዎች፣ ገደሎች አሉብንና በእንቅርት ላይ ... እንዳይሆን አበክረን ልንጠነቀቅ ይገባል ። ከጊዜያዊ ድል ዘላቂውን የሀገርና የሕዝብ ጥቅም ማስቀድም ትልቁን የተስፋ ስዕል አሻግሮ ማየት ያስፈልጋል ።

ታዋቂው አሜሪካዊ የጥቁሮች መብት ተሚጋችና የሰላማዊ ትግል ሐዋርያ ማርቲን ሉተር ኪንግ "... እያንዳንዳችንን በቀጥታ የሚጎዳ ሁላችንንም በተዘዋዋሪ ይጎዳል። ..."ሲል የተናገረው ሰሞነኛውን አውድ ይዋጃል ብዬ ስለአሰብሁ አጋርቼ ፤ በመጀመሪያ አቦ ድርቢ በመቀጠል አቦ ሙሉጌታ አምና ባስተላለፉት አባታዊና ወንድማዊ ዘመን ተሻጋሪ ምክር መጣጥፌን ልቋጭ ። "... ባለቤቱ የእኔ ነው በማለት ትልቅ ቦታ የሰጠውን በማጣጣል ጣትን መቀሰር አይገባም ።"

ከሁሉም በላይ ኢሬቻንም ሆነ መስቀልን በዓመት አንድ ጊዜ በአደባባይ ማክበር ብቻ ሳይሆን በዕለት ተዕለት ኑሯችን እንተርጉማቸው ። እንኑራቸው ። በልካቸው እንገኝ ። ልካቸው ሰላም ፣ እርቅ ፣ ይቅርታ፣ መቀባበል ፣ መግባባት ፣ አብሮነት ፣ አንድነትና ሰው ሆኖ መገኘት ነውና ።

ፈጣሪ የከርሞ ሰው ይበለን !

አሜን ።

ማህበራዊ

# የሕይወት ገጽታ

## ‹‹የወታደር ልጅ ነኝ› - ዮሀና ረታ

ጽጌረዳ ጫንያለው

ተስፋ መቁረጥን መቼም ቢሆን ሞክራው አታውቅም:: በብዙ ፈታኝ ችግሮች ውስጥ እያለፈች እንኳን ነገን በተስፋ አሻግራ ትመለከታለች:: ለዛውም ደማቅ ተስፋ:: ዛሬን ከነገ የሚያሻግር ብሩህ ተስፋ:: እሷ የዘወትር ጥንካሬዋ ካሰበችው ያደርሳታል:: በእርግጥ እርምጃዋ ሁሉ ሰውን የሚያስቀድም ነው:: በተለይ በሕጻናት ላይ ያላት ልዩ ፍላጎት የማይታሰበውን ተራራ እንድትንደው አድርጓታል:: ዮሀና ረታን::

ዮሀና ይሁን ብላ ካመነች የራሷን መልካም እድሎች ጭምር እርግፍ አድርጋ ትተዋለች:: ለምን ካሉ እርሷ ለበጎነት ስትል የምትሰስተው የላትምና:: ይህንን ውሳኔ የተማረችው ደግሞ ከወታደሩ አባቷ ነው:: ወታደሩ አባቷ ለውድ አገራቸው ሕይወታቸውን ሰውተዋል:: ከዚያ አስቀድሞ ግን ልጆቻቸው አገር ወዳድ ሆነው እንዲያድጉ ቀርጸዋቸዋል:: ዛሬ ዮሐናም ይህን ፈለግ ተከትላ ለአገርና ለወገኗ የማትከፍለው የለም::

ትውልድና እድገቷ ከአዲስ አበባ በቅርብ ርቀት ከምትገኘው ለምለሚ ስፍራ ቢሾፍቱ ነው:: ብዙውን የልጅነት ጊዜዋን በዚህች ውብ ከተማ አሳልፋለች:: አባቷን ሰባት ዓመቷ ላይ በማጣቷ ብቻቸውን ባሳደጓት እናቷ እቅፍ ውስጥ ሆና ትምህርቷን እስከ ሁለተኛ ደረጃ ተከታትላለች::

### የወታደር ልጅነት በረከት

አባቷ ለአገር ብለው ቢሰዉም ብዙ መልካም እሴቶች እንደሰጧት ታምናለች:: የመጀመሪያውና ቅድሚያ የሚሰጠው ደግሞ ሰውን አብዝቶ መውደድን ነው:: እሷ በሰው መውደድ ውስጥ አገር መውደድን አይታለች:: አባቷ ስለ አገር ፍቅር መስበክ የሁልጊዜ ልምዳቸው ነበር::

ዮሀና አባቷን ማጣቷ ቢሰማትም ዓላማ ያላት ልጅ ሆናለች:: ይህ እውነታም ስለሀገሯ የምትከፍለው ዋጋ እንዲኖርና እንዲሰማት አድርጓል:: ከአባቷ ማንነት ለአገር ብሎ መሰዋት ትልቅ ክብር እንዳለው ተረድታለች:: አባቷ በሕይወት በነበሩ ጊዜ ከእርሷ ጋር ቅርብ ቁርኝት ነበራቸውና የወታደር ሕይወትን በደንብ አስተምረዋታል:: ሀገርን ለማስረከብ ሕይወታቸውን እንደገበሩም ታውቃለች:: እናም ወታደርነትን አጥብቃ ትወዳለች::

እርሷ ወታደር ባትሆንም ውትድርናን ኖረዋለች:: የወታደር ልጅ በመሆኗ በስነምግባር መኖርን ታውቃለች:: በራስ መተማመንን አዳብራለች:: ራሷን እንደሴት ብቻ ሳይሆን እንደጀግና አይታ እንድትጓዝም ሆናበታለች:: ተስፋ መቁረጥን እንዳታስብ ፤ በተለይ ደግሞ ‹‹አልችለውም›› ይሉትን ዕንቅፋት እንዳታስብ ወስናለች::

ከራስ ፍላጎት አልፎ ለሌላው መቆምና መሥራት የሚለውንም ያገኘችው የወታደር ልጅ በመሆኗ ነው:: ከዚያ ባሻገር የወታደር ልጅ በመሆን ውስጥ ጽናትን ተላብሶ መኖርን አውቃለች:: ‹‹ወደፊት እንጂ ወደኋላ እንዳታይ›› የሚለውን እውነታ አረጋግጣለች:: ዮሀና ከዚህ በተያያዘ አንድ እውነታ ታነሳለች:: ‹‹ወታደር ቤተሰብ ሲኖረን ሞትን አንፈራም:: ይልቁንም በዚህ ውስጥ ያለውን መሥራትና ታሪካዊ አሻራን ማኖርን እናስባለን እንጂ:: ›› የሚለውን ሀቅ ::

ይህ ብቻ አይደለም ‹‹ሕልም ሁሉ ዓላማ ያለው እንደሆነ አምነን ለጊዜ ዋጋ እንሰጣለንም:: ዛሬ፤ ነገ ወይም ከነገወዲያ እሞታለሁ የሚለው ውስጣችን ስለሚኖር ከፍርሃት ሳይሆን ከትጋት አንጻር ደቂቃዎችን መጠቀም እንጀምራለን:: በዚህ ውስጥ ስናልፍ ደግሞ እያንዳንዱ ቀን የሥራና የውጤት ይሆንልናል›› ትላለች::

የወታደር ልጅ መሆን ድፍረትን ለራስ መስጠት ነው:: ችግር ሳይሆን በችግር ውስጥ ድል እንዳለ ማሰብም ነው:: ቀናትን የታሪክ መተኪያም እያደረጉ ማለፍ ነው:: ለዚህ ደግሞ በእነርሱ ቤተሰብ ውስጥ ያለው የወንድና የሴት ሥራ አለመለያየት ትልቅ አስተዋፅዖ እንደነበረው ታነሳለች:: ሁሉም ለሁሉም መሥራትና መለወጥን:: በዚህ ውስጥም ሰው ገንዘብና ውርስ ባይኖረው እንኳን ንጹህ ልብ ካለውና የመሥራት ፍላጎትን ካነገበ ስኬቱ ላይ ይደርሳል የሚለውን አረጋግጦላታል::



ፎቶ፡ ሃዲስ አብርሃ

### ትምህርት ከሥራ ጋር

በትምህርቷ ቤተሰቧ ተስፋ የሚጥልባት ልጅ ነበረች:: ለእህቶቿም ሆነ ለወንድሞቿ ከእርሷ በላይ አርኣያ የሚሆን እንደሌለ ሲተማመኑባት ቆይተዋል:: እሷም 12ኛ ክፍል እስከትደርስ ጉብዝናዋን አረጋግጣለች:: የደረጃ ተማሪ በመሆኗም ቤተሰቧን አስመሰግናለች:: በመምህራኖቿ ዘንድም ቢሆን ምስጉንና ተወዳጅ ተማሪ ነበረች:: ማትሪክ ከወሰደች በኋላ ግን ነገሮች ተቀየሩ:: ተስፋ አስቆራጭ ችግር ገጠማት:: ውጤቷ የታሰበውን ያህል ሊሆን አልቻለም:: ለዩኒቨርስቲ የተጠበቀችዋ ልጅ ከቤቷ ቀረች:: የዚህን ጊዜ ሰማዩ በላይዋ የተደፋ አስኪመስላት ነገሮች ከበዷት:: ምን ማድረግ እንዳለባት ግራ ተጋባች::

ዮሀና ጭንቀትና ሀፍረት ውስጧን አደማው:: በተለይ አጋጣሚዎች የአባቷን ቃል እንዳሳጠፏት ባሰበች ጊዜ ሕመሟን ባሰባት:: ስማቸውን በአገር ብቻ ሳይሆን በዓለም አደባባይ አስጠረዋለሁ የምትለው ልጅ የዩኒቨርስቲ ውጤት ማምጣት አለመቻሏ በእጅጉ አበሳጫት:: እናም በቶሎ ትምህርት ቤት ላለመግባት ወስና ራሷን ለማረጋጋት ትጣጣር ጀመር::

እናቷና ወንድም እህቶቿ በብዙ ጎዶሎዎቿ ከጎኗ እየተገኙ ደገፏት:: ችግሩንም እንድትረሳው፣እንዳታስበው አደረጓት:: ከቤተሰብ ሳትርቅ ቢሾፍቱ ከተማ ሆና ለመማር ወሰነች :: በዲፕሎማ አካውንቲንግ ለመማርም ተመዘገበች:: የዲፕሎማ ትምህርቱንም በቁምነገር ያዘችው:: ትኩረት ሳትነፍግ አጥብቃ እየተከታተለች መማሯን ቀጠለች:: በዚህ ጥረቷ ግን እስከመጨረሻው አልገፋችበትም:: ከያዘችው በላይ የምታስቀድመው ሌላ ጉዳይ ከዓይኖቿ ገቡ :: የልጆችን ስቃይ እያዩ የራስን ምቾት ማደላደል ትክክል እንዳልሆነ ያሳሰባት ያዘ::

> **እርሷ ወታደር ባትሆንም ውትድርናን ኖረዋለች:: የወታደር ልጅ በመሆኗ በስነምግባር መኖርን ታውቃለች:: በራስ መተማመንን አዳብራለች:: ራሷን እንደሴት ብቻ ሳይሆን እንደጀግና አይታ እንድትጓዝም ሆናበታለች**

እሷ ዲፕሎማ እየተማረች በነበረ ጊዜ በርካቶች በትምህርት እድልም ይሁን በሌላ አጋጣሚ ውጭ አገር መውጣትን የሚመኙበት ጊዜ ነበር፣ አብዛኞቹም ከራሳቸው በላይ ሌሎችን ለማየት አይደፍሩም ::

ዮሀና ከሰዎች ጋር የመግባባት ችሎታዋ የተለየ በመሆኑ ወዲያው የፈለገችውን አግኝታ ነበር:: በዛን ወቅት ከደኞች ወይም ከኔዘርላንድ ተወላጆች ጋር ትግባባለች :: ይህ አጋጣሚም ምን እናድርግልሽ ሲሉ ላቀረቡላት ጥያቄ ከቁሳዊ ፍላጎት ይልቅ ትምህርቷን እንደምታስቀድም ትገልጽላቸዋለች :: ዮሀና ውጭ አገር ሄዳ መማር እንደምትፈልግ ትናገራለች:: ፈቃዳቸውን በሰጧት ጊዜም ሂደቱን ጀመረች:: በዚህ መሐል ግን እነዚሁ ሰዎች ሌላውን ነገር አሳሰቧት::

ሰዎቹ ኢትዮጵያ በቆዩባቸው ጊዜያት በርከት ያሉ ሕጻናትን በችግር ሲማቅቁ አይተዋል:: በዚህም ልባቸው ሲያዝንና ውስጣቸው ሲጨነቅ ቆይቷል:: ይህን ስሜት ይዘው ምን ማድረግ እንዳለባቸው ዮሀናን አማከሯት:: ይህ እውነት የበርካታ ልጆች ታሪክ ነው:: ችግሩ የእነሱ ሳይሆን የእሷና የሌሎች ወገኖች ግዴታ ሊሆን ይገባል::

ዮሀና ጉዳዩን ስታወጣ ስታወርድ አድራ ይበጃል ያለችውን ሀሳብ አቀረበችላቸው:: ይህም የእነሱ እገዛ ሳይለያት NGO አቋቁማ እነርሱን እየደገፈች መኖር እንደምትሻ የሚያበስር ነው:: ሰዎቹ እጅጉን ተደስተው በሀሳቧ ተስማሙ:: እንዳለችው ከጎኗ ቆመው ሥራውን ጀመሩ ኃላፊም፤ መሥራችም ሆና መሥራቱን ቀጠለች በዚህ መሀል ስትጓጓለት የቆየችው የትምህርት እድል ምላሹን አገኘ :: ዮሀና ውጭ ሀገር ተጉዛ የተሻለውን ትምህርት የምታገኝበት፣የልጅነት ሕልሟንና የአባቷን ፍላጎት የምትሞላበት ጊዜው ደረሰ:: አሁን በትናንቱ አለመሳካት አትቆጭም:: ባለፈው ታሪክም አታዝንም:: ይህ ዕድል ለእሷና ለመላው ቤተሰብ ዕንባን ከዓይኖች ያብሳል:: የሳቅ ዘመንን ያውጃል::

ዮሀና ዘንድ ያደረው ስሜት ግን ብዙዎች ከሚያስቡት የተለየ ሆነ:: እሷ ይህን ዕድል እንደትናንቱ ልትቀበለው አልወደደችም:: ከራሷ ምቾት ይልቅ የሌሎችን አስቀደመች:: ከእኔ ዓለም የሌሎች ይቀድማል ስትል ዲፕሎማ መማሯን አቁማ ፤ ውጪ አገር መጓዙን ትታ ለዓመታት ድርጅቱን በኃላፊነት ለመምራት ወሰነች፤ አደረገችውም ::

ዮሀና ከዓመታት የሥራ ላይ ቆይታ በኋላ ነው ሁኔታዎች ከትምህርት ውጪ መሆን እንደሌለባቸው ቢገባት መማሯን ቀጠለች :: ዩኒቨርሲቲ ገብታም ከአንድም ሁለት ዲግሪዎችን ያዘች ::

### ፈተናና ጣፋጩ ድል

ዮሀና 12ኛ ክፍልን እንዳጠናቀቀች ያለፈችባቸው አጋጣሚዎች ነገሮችን በተለየ ዓይን እንድታይ አድርጓታል:: እንዲህ መሆኑ ደግሞ የልጅነት ሕልሟን ለማሳካት ጭምር በር ከፍቶላታል:: በእርግጥ ይህም ቢሆን ቀላል ውሳኔን የሚጠይቅ አልነበረም:: አጋጣሚው የራስ እድልን ለሌላ እስከመስጠት በሚያደርስ ውሳኔ የተሞላ ነበር:: በወቅቱ ዮሀና ከተቀረጸችበት ማንነቷት ጋር ነበረች:: ሰውን መርዳት የኖረችለት ዓላማዋ ነውና አድርጋዋለች:: ‹‹ከትምህርቴ ሰውን መርዳት ይበልጣል›› ስትል ያገኘችውን ውጭ አገር ሄዶ የመማር እድል መልሳለች:: እንዳሰበችው ከሀገሯ ቀርታም ልጆችን የመታደግ ሥራዋን አሳክታለች ::

በራሷ ውሳኔ መርጣ መሐን የሆኑ ኔዘርላንዳዊ ባልና ሚስቶች እርሷን ጭምር እንደ ልጅ እያዩዋት የሀገሯን ልጆች እንድታግዝ አድርገዋታል:: ሕልሟ ስለተሳካላት የሚታገዙ ፤ ልጆችን ይዛ ከስምንት ዓመታት በላይ ሠራች:: ሕጻናትን የመርዳት ጉጉቷንም

# የሕይወት ገጽታ



**እንደ ሀገር የለንም የሚባለው ያልተማረ ሰው ሳይሆን የተማረው ሰው ሀገሩን፣ ኅብረተሰቡን የሚያይበት ዓይን ነው:: የተማረው ዜጋ ሀገሩንና ሕዝቡን መውደድ አለበት**

አሳካች:: በዚህ ውሳኔዋ ዛሬም ድረስ ደስተኛ ናት::

ዮሀና ለችግር የተጋለጡ ልጆችን ለማገዝ በእርሷ አነሳሽነት የተቋቋመውድርጅት ሴቭ ሄቨን የሚባል ነው:: የመጀመሪያዎቹን ዓመታት ሰዎችን በማገዝ ዙሪያ አተኩራ ሥትሠራበት ቆይታለች:: ድርጅቱን በምትመራበት ወቅት የቤተሰብ ፍቅር ብቻ ሳይሆን የሚፈልጉትን ዓመታዊ ድጋፍ የምታደርግላቸው 400 ልጆች ነበሯት :: ኤች.አይ.ቪ. ፖዘቲቭ የሆኑ ሴቶችንም እንዲታገዙ አድርጋለች:: እነዚህን ሴቶች ከአልጋቸው ተነስተው ለልጆቻቸው እንዲደርሱ በብዙ ደግፋቸዋለች::

ድጋፉ የሚያተኩረው ለሴቶቹ የመጀመሪያ ስልጠና በመስጠት ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ መንቀሳቀሻ ካፒታል እንዲያገኙ በማድረግ ነው:: በዚህ ደግሞ ብዙ ፍሬያማ ልጆችን ለአገር እንዲያበረከቱ አድርጋለች::

እነዚህ ሴቶች በመንግሥት በኩል የመጡ ሲሆኑ፤ በልደታ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 15 ወይም ትንባሆ ሞኖፖል አካባቢ የሚኖሩ ናቸው:: መንግሥት ቢሮ ሰጥቷትም ነው ሥራውን ስትሠራ የቆየችው:: ሁሉም የሚሹት ተሟልቶላቸው ጥሩና ስኬታማ ተማሪዎች እንዲሆኑ አስችላቸዋለች::

ዮሀና ‹‹ተሰጥዖ ማለት ለተጠሩበት ዓላማ መኖር መቻል ነው›› የሚል እምነት አላት:: በዚህ ውስጥ ደግሞ እርካታ ብቻ ሳይሆን ማንነትን ማወቅ ይቻላል ባይ ነች:: እርሷ ተሰጥዖዋን ማወቋ ለዛሬ መልካም ጉዞዋ መንገድ ጠርጋበታለች:: አምላክ ለሁሉም አንድ አይነት ነገር አይሰጥምና ለሰው መኖርን የተሰጣት በረከት እንደሆነ አረጋግጣለች:: በዚህም እናትና አባት የሌላቸውን 12 ልጆችን አሳድጋ ለወግ ማዕረግ አብቅታለች:: ልጆቹ ምንም አይነት ዘመድ የላቸውም:: እርሷ ግን ዘመድ ሆናቸዋለች::

ሁሉም ልጆች እንደሌሎች ሕጻናት የልደት ቀናቸው አይታወቅም :: እርሷ ግን ለእያንዳንዳቸው የውልደት ቀን አበጅታላቸዋለች:: ስማቸውን ሳይቀር ያወጣችላቸው ራሷ ናት:: እናትም ፣አባትም፣ ዘመድም ሆና ተንከባክባቸዋለች::

ለአገሯ ልጆች ያልከፈለችው መስዋዕትነት የለም:: ከልጆቿ በላይም ለእነርሱ ዋጋ ሰጥታለች:: ለልጆቹ የራሷን ዕድል አሳልፎ ከመስጠት ባሻገር የትምህርት ቁሳቁስና አጠቃላይ ምግባቸው ተችሏቸው እንዲማሩ አስችላለች:: የራሷን ልጆች ስታሳድግ በባለቤቷም ሆነ በቤተሰብ በኩል ድጋፍ ይኖራል:: በዚህም ደግሞ ሸክሟ ቀላል ይሆናል:: ወላጅ የሌላቸው ልጆችን ማሳደግ ግን ከዚህ እውነት ይለያል:: ለእነዚህ ልጆች ድጋፍና እንክብካቤ ማድረግ ግን ታላቅ አደራን እንደመሸከም ነው:: በዚህም ኃላፊነቴን በመወጣቴ ደስተኛ ነኝ ትላለች::

ዮሀና ወደዚህ ሥራ ስትገባ ገና በ18 ዓመቷ በመሆኑ ማንም ስኬታማ ትሆናለች ብሎ አልጠበቃትም :: ነገሮችን የመራችበትና ስትሠራበት የቆየችበትን ሁኔታ ሲመለከቱ ግን በርካቶች ያደንቋት እንደነበር አትረሳም:: ይህ እድሜ እንደሚታወቀው ከቤተሰብ እንኳን የማንላቀቅበት ነው:: ትምህርትንም ለማጠናቀቅ ብዙ የሚለፉበት ጊዜ እንደሆነ ግልጽ ነው::

ዮሀና በዚህ እድሜዋ ለሌሎች ተስፋ ሆናለች:: ለአገር መልካም የሆኑ ዜጎችን ፈጥራለች:: በዚህም ሁልጊዜ ደስ ይላታል :: ይሁንና የሚሠራ ሲኖር ነገሮች ፈተና የሚሆኑበት አጋጣሚ አይጠፉምና ይህንን መልካም ሥራዋን የሚያጨልምባት ክስተት ተፈጠረ:: ይህም በመንግሥት በኩል ለ NGO ድርጅቶች የወጣው የ70፤ 30 መመሪያ ነው::

ይህ መመሪያ ነገሮችን ድብልቅልቅ አደረገባት:: የምትወዳቸውንና የምትንሰፈሰፍላቸውን ልጆች እንድትበትን አስገደዳት:: ለዚህ ደግሞ መንስኤው የእርሷ የገቢ ምንጭ የውጪ አገር ዜጎች መሆናቸው ነበር :: እናም በራሷ አቅም ነገሮችን ማስቀጠል ስለከበዳት ያሏትን አነስተኛ ልጆች ለሌላ ድርጅት በመስጠት ለጊዜው ሥራውን አቆመች:: ከዓመታት በኋላ ግን የሕልሟን ጥሪ ዳግም ጀመረችው::

አሁን ‹‹ኬር ፎር ጀነሬሽን ዴቨሎፕመንት ቻሪቲ›› የሚባል ድርጅት ከፍታ በመሥራት ላይ ትገኛለች:: ድርጅቱ እንደቀድሞው ሁሉ ሕጻናትና እናቶች ላይ ልዩ ትኩረቱን አድርጎ የሚሠራ ነው::

የመጀመሪያው NGO ሲዘጋ የሥራ ዘርፏን የቀየረችው ባለታሪካችን፤ የትምህርት ዘርፉን ለመቀላቀል ችላለች:: ይህም ዘርፍ ሌላ ፈተና ያለበት ቢሆንም እንደርሷ ግን ይህ ፈተና የሚሆንበት አጋጣሚ የለም ባይ ናት:: ስለዚህም ሥራውን ኮሌጅ ከፍታ በመሥራት ጀምረዋለች:: ኮሌጁ ‹‹ጎልደን ስታር›› ይባላል:: ዋና ትኩረቱም ማኅበረሰቡን ማገልገል ነው:: ኮሌጁ በተለያየ ችግር ላይ ያሉ ዜጎችን በማገዝ እየሠራ ይገኛል:: እንደሷ ዕምነት በተለይ አቅም ኖሯቸው መማር ያልቻሉ ሴቶችና አካል ጉዳተኞች ችግር እንዲገጥማቸው አትፈልግም:: ስለዚህም እነርሱን ማገዝ ባለባት ልክ እያገዘች በመሥራት ላይ ትገኛለች:: ፖሊሶችንና በማረሚያ ቤት የሚገኙ ወገኖችን በቅናሽ ዋጋ የመማር እድል እንዲያገኙ አመቻችታለች:: በተመሳሳይ የዓመት ሙሉ የክፍያ ወጪያቸውን በመሸፈን እስከ 20 ሰዎችን በነጻ ታስተምራለች::

ሌላው የሠራችውና ለውጥ እያመጣችበት ያለው ተግባር ደግሞ በማማከር ላይ የምትሠራበት ድርጅት ነው:: ድርጅቱ ጎልደን ብሪጅ ትሬኒግ ኤንድ ኮንሰልታንሲ ፒኤልሲ በመባል ይጠራል:: ስብሰባና ኮንፍረንሶችን በማዘጋጀት ጭምር የሚሠራ ድርጅት ነው:: የማማከር ሥራው በዋናነት ትኩረቱን የሚያደርገው ከለውጥ ሥራ ጋር በተያያዘ ነው:: ሥራ ፈጠራና ሴቶችን ማብቃት፣ እንዲሁም ወደአመራርነት ማምጣት ላይ ትኩረት ያደርጋል :: በዚህም እስካሁን በትምህርቱ ዘርፍ እንደሠራችው ባይሆንም በርካታ ተግባራትን ከውናለች:: በተለይም ከሴቶችን ጋር ተያይዞ ለውጥ ያመጣችባቸውም ቦታዎች እንዳሉ ታነሳለች::

ዮሀና በዚህ ዘርፍ በሲዳማ ክልል ፖሊስ ኮሚሽን አካባቢ የተሠራውን ተግባር በምሳሌነት ታነሳለች :: ሴቶቹ ስልጠና እንዲወስዱ በማድረግ ከነበሩበት ደረጃ ወደ አመራርነት ጭምር እንዲመጡና ከፍ እንዲሉ ማገዟ አንዱ መሆኑን ትጠቅሳለች::

ዮሐና « የእኔ ስኬት በእኔ ሰበብ ሌሎች መኖር ሲችሉ ነው›› የሚል እምነት አላት:: ይህንን ደግሞ በእውቀት አዳብራ መሥራት ትፈልጋለችና አድርገዋለች:: ከራሷ ፍላጎትና ከራሷ ምቾት ይልቅ ሌሎችን አስቀድማም አሳይታለች:: እንደእርሷ እምነት ሰው ለሰው ኖርኩ ሲል ከአለው ምቾቱ ላይ ቀንሶ ለሌሎች ማካፈል ሲችል ነው:: የዚያን ጊዜ ለእነርሱ ብቻ ሳይሆን ለራሱም የሚደርስ ስኬትን፣ደስታን ያገኛል:: ይህንንም በራሴ አይቸዋለሁ ትላለች:: ስኬት ላይ ግን አልደረስኩም እንደውም ገና ዳዴ እያልኩ ነው ባይ ነች:: ብዙ የምሠራቸውና ለሀገሬ የማበረክታቸው ነገሮች አሉኝ፤ ሀገሬና ፤ አባቴ የከፈሉልኝን ዋጋ ገና አልጀመርኩትም ትላለች ::

### አሁናዊ ሁኔታ

ወይዘሮ ዮሀና ጎልደን ስታር ኮሌጅን በኃላፊነት ትመራለች:: ሌላው ጎልደን ብሪጅ ትሬኒንግ ኤንድ ኮንሰልታንሲ ፒኤልሲ እንዲሁም ‹‹ኬር ፎር ጀነሬሽን ዲቨሎፕመንት ቻሪቲ ›› በመከፈት ድርጅቱን በዳይሬክተርነት እየመራች ትገኛለች:: በሦስቱም የሥራ ዘርፎች ላይ ለ70 ሠራተኞች የሥራ እድል ፈጥራለች::

ጎልደን ስታር ኮሌጅ በሀዋሳ ፣ በሆሳዕና እና በአዲስ አበባ ከተሞች በመሥራት ላይ ይገኛል:: በቅርቡ ደግሞ በሐዋሳ ሁለተኛውን መደበኛ ቅርንጫፉን ይከፍታል::

### ቀጣይ ህልም

ዮሀና በትምህርት ዘርፉ የተሻለ መሥራት የመጀመሪያው እቅዷ ነው:: እንደ ሀገር የለንም የሚባለው ያልተማረ ሰው ሳይሆን የተማረው ሰው ሀገሩን፣ ኅብረተሰቡን የሚያይበት ዓይን ነው:: የተማረው ዜጋ ሀገሩንና ሕዝቡን መውደድ አለበት:: ስለዚህም ስብዕና ግንባታ ላይ ፍሬያማ ሥራ ማከናወን ትፈልጋለች:: በተጨማሪም አቅም ያላቸው ሴቶችን ማፍራት :: ለዚህም የተለያዩ ስልጠናዎችን በግልም ሆነ በተቋም መስጠት፣ የሚማሩበትን እድል ማመቻቸት ዓላማዋ ነው::

ወጣቶች ከሱስና ከመጥፎ ተግባራቸው ወጥተው የራሳቸው ሥራ ፈጣሪ እንዲሆኑ ማስቻል ላይም የመሥራት ፍላጎት አላት :: እናቶችን የማመስገኛ ቀን በቋሚነት የማዘጋጀትና እንዲታገዙ ማድረግ ላይም እቅድ አላት:: በተመሳሳይ ወጣቶች በተለይም ተመራቂ ተማሪዎች ደም እንዲለግሱ በማበረታታት አገር ወዳድነታቸውን እንዲያሳዩ የማስቻል ዓላማን ሰንቃለች:: ይህም ከዘንድሮ ዓመት ጀምሮ ተግባራዊ ለመሆን ዝግጁ ነው ::

### መልዕክት

ሰዎች ስኬታማ ለመሆን ሦስት ነገሮችን አጥብቀው መሻትና ወደተግባር መቀየር አለባቸው:: የመጀመሪያው የሚሠሩትን ነገር መምረጥና ለዚያ ነገር ራሳቸውን ማዘጋጀትና ማሳመን ሲሆን፤ ሁለተኛው የሚመጡ እድሎችን ወደ ዓላማው መቀየር የሚለው ነው:: ከሌሎች ሳይሆን ከራስህ ለራስህ እድልን ተጠቅሞ ወደ ዓላማ ማምጣትን ማሳየት ያስፈልጋል:: በተለይም የራስን እድል በራስ ለመወሰን መትጋት ይገባል::

ዛሬ እያጨድን ያለነው የዘራነውን ነው:: ትውልድ ላይ ያለመሥራት ውጤት መልካም ነገሮቻችንን ጭምር ያወድምብናል:: ማንነታችንንም ያስረሳብናል:: ደፋር፣ አገር ወዳድ፣ ባለታሪክ፣ ጀግና፣ እንግዳ ተቀባይ የምትባለው ኢትዮጵያ በግጭት መነሳት የጀመረችውም ለራሳችን ብቻ በመጨነቅ ውስጥ ተዘፍቀን ሌሎችን ማየት ባለመቻላችን ነው::

እናም ዛሬን ዛሬ ላይ ችግራችን እንዲያከትም ከፈለግን፤ ግጭቶች እንዳይቀጥሉ ካሰብን ትምህርቱ ዘርፍ ላይ ከጥራቱ ባልተናነሰ መልኩ ሥነምግባር ላይ መሥራት አለብን:: የዚያን ጊዜ ሀገርን የሚወደውን ዜጋ እናገኘዋለን፤ ከአገሩ አልፎ ለዓለም ተስፋ የሚሆነውን ትውልድ እናየዋለን ስትል መልዕክቷን ታስተላልፋለች::

የትምህርት ተቋም ትውልድ የሚቀረጽበት ቦታ ነው:: ትውልድን ስናነሳም ሀገርን ማንሳታችን አይቀርም:: ስለዚህም ሀገርን መገንባት ተደርጎ መወሰድ አለበት:: በተለያዩ አገራት የመዞር አጋጣሚው ነበረኝና ማንም ዜጋውን ሳይሠራ ሀገሩን እንደማይገነባ ተረድቻለሁ:: ስለዚህም የትምህርት ተቋማት የሚያስተምሯቸውን ተማሪዎች ሀገራቸውን እያሰቡ መሥራት አለባቸው የሚል እምነት አለኝ:: እኔም በዚያ ልክ እየሠራሁ እገኛለሁ:: አባቴ የሚወዳትና የሞተላትን አገር እኔም መታደግ አለብኝና በትምህርት ጥራቱ የተሻለች እንድትሆን እተጋለሁ ::

የከፈትኩት ኮሌጅ ስያሜ ‹‹ወርቃማ ኮከብ›› ነው:: ወርቅ ለማግኘት ደግሞ ከባድ ልፋትን ይጠይቃል:: እናም የእኔ ኮሌጅ ዓላማ ተማሪዎች ወርቃማ ኮከብ ሆነው ለአገራቸው ብሎም ለዓለም እንዲያበሩ ማድረግ ነው::

እውቀት የሚገዛም የሚሸጥም አይደለም:: ትምህርት የንግድ ቦታ አይደለም:: ማንኛውም መሥሪያ ቤት ሄደን ለአገልግሎት እንደምንከፍለው ሁሉ በዚህም ለመምህራንና ለሌሎች ወጪዎች የሚሆን ገንዘብ ከፍለው እንዲማሩ ይደረግበታል እንጂ :: ስለዚህም ትምህርት ንግድ ሳይሆን ትውልድን የማውጣት አደራ ነውና ያንን አስበን እንሥራ መልዕክቷ ነው::

# "'ያሆዴ'' የምስጋናና የተስፋ በዓል

**መሳኩ ኤሮሴ**

ሀዲያ ከጥንት ጀምሮ የበርካታ እሴቶች ባለቤት ሲሆን፤ በረጅም ታሪካዊ ሂደቱ ይዞ ካቆያቸው ባህላዊ ዕሴቶቹ አንዱ የ"ያሆዴ" በዓል ነው። "ያሆዴ" በሀዲያ ብሔር ዘንድ ከሚከበሩ በዓላት መካከል በክዋኔዎቹ ስፋት፣ በዘመን ተሻጋሪነት፣ በውስጡ በያዛቸው ባህላዊ እሴቶችና ማኅበራዊ ፋይዳው ቀዳሚነቱን የሚይዝ ትልቅ ክብረ በዓል ከመሆኑም ባሻገር በብሔሩ ተወላጆች ዘንድ ያለ ሃይማኖት ልዩነት በልዩ ድምቀት እና በአንድነት ከሚከበሩ ቱባ በዓላት አንዱና ቀዳሚው ነው።

"ያሆዴ" የሚለው ቃል በያሆዴ በፕሮግራም ከሚቀነቀነው ዘፈን ሁለት ቃላት የተመሠረተ ነው፤ ቃሎቹም «ያሆሆሆ_ያሆሆ ያሆዴ- ያሆሆ» ሲባል ያሆሆ የሚለው ድምጽ የዘፋን የድምፅ ቅላጼ ሲያመላክት ኤዴ የሚለው ደግሞ ማገናኘትን፣ ማጣመርን፣ ማያያዝን ያመለክታል።

"ያሆዴ" ከአዲስ የልምላሜ፣ የብርሃን፣ የፍካት፣ ብሩህ ተስፋ፣ ሰላም እና ደስታ ካለበት ዘመን ጋር ማገናኘቱን / ማጣመሩን/ የሚያመለክት ቃል መሆኑን የሀዲያ ብሔር ባህልና ቋንቋ ተመራማሪ እና የሀዲይሳ መጽሐፍት ጸሐፊ አቶ ግርማ ሱልዶሎ ይናገራሉ።

እንደ አቶ ግርማ ማብራሪያ፡ የጥንቱ የሀዲያ አባቶች ዝናብ፣ ጤዛ፣ ውርጭ፣ ቅዝቃዜ ሳይበግራቸው የሚያርሱ፤ በሄክታሮች የተዘራውን በቆሎና ማሽላ በግልና በሕብረት /Geja/ የሚኮተኩቱ፤ ቀኑን ሙሉ ተቀምጠው እንዳጎነበሱ ጤፍ የሚያርሙ፣ በክረምቱ ጭቃ፣ ጤዛ፣ ዝናብ ከብቶቻቸውን በመከራ እንደሚያግዱ እረኞች መንፈሰ ጠንካሮች ነበሩ። ከወንዝ ሙላት የተነሳ ገበያ፣ ለቅሶ፣ ዘመድ ጥየቃ ለመሄድ የዋና ስልቻን ጭምር ፈጥሮ ለመጠቀም ቢሞከርም ያስከፍል የነበረው ዋጋ እጅግ ከባድ ነበር።

ከብቶቻቸው ሜዳ ላይ ሲሰማሩ ተናዳፊ ዝንብ ሻኛቸውንና ጀርባቸውን እያቆሰላቸው መቆሚያ የሚያሳጣ ቸሬኤ የተሰኘው ወፍ በነፍስም ጭምር ዋጋ የሚያስከፍል የሦስት ወራት እልህ አስጨራሽ ትግል አብቅቶ፤ በፀደይ ወቅት መነሻ በመስከረም (ሞሶሮአ) ወር የሚታየውን የአበባ ፍካት፣ የሳር ቅጠሉ ልምላሜ፣ የአዝመራው ልምላሜ አንዳንዱም ማሸት የጀመረበት፣ ንቦች በዜማ በአበቦች ላይ እየተመሙ የሚቀስሙበት ዘመን መነሻ መሆኑን ያነሳሉ።

ወሩ ከፊት ለፊት ያለውን ብሩህ ተስፋ፣ በመሰነቅ ከአሮጌው ዓመት ወደ አዲሱ ዓመት የመሻገር ጊዜ ማሳያ በመሆኑ የጥንቱ ሀዲያ መስከረምን ለዘመን መለወጫነት እና ለቀን መቁጠሪያ መነሻነት ሲጠቀም ክብረ በዓሉን ደግሞ እጅግ በደመቀ ሥነ ሥርዓት ሲያከብር ቆይቷል።

የያሆዴ በዓል ሙሉ ይዘት ይዞ መከበር የጀመረበት ትክክለኛ ቀን፣ ዓመት፣ ወቅት በወል እንደማይታወቅ በዘንድሮው ያሆዴ በዓል ዋዜማ በሲምፖዚየም ላይ በቀረበው ጥናታዊ ጽሑፍ ላይ ተጠቅሷል። ያሆዴ በዓል የመጀመሪያ ፈጣሪ ሰው የማይታወቅ ሲሆን ፣ጥንታዊ የሆነው ሀዲያ በዕድገት ሂደቱ ክህሎቱን ተጠቅሞ የፈጠረና ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲሸጋገር የመጣ ጥንታዊ በዓል መሆኑን አቶ ግርማ ሱልዶሎ ይናገራሉ።

የያሆዴ በዓል በርካታ ፋይዳዎች እንዳሉት የሚያነሱት አቶ ግርማ፤ ያሆዴ የአዲስ ዘመን ማወጃያ፣ የዘመን መለወጫ እና የቀናት መቁጠሪያ መነሻ ማብሰሪያ ነው ይላሉ። በሀዲያ ሕዝብ ዘንድ ሰዎች ቀን መቁጠር የሚጀምሩት ያሆዴ ከወጣበት ቀን አንስቶ ነው።

ያሆዴ የዘመን መለወጫ እና የቀናት መቁጠሪያ መነሻ ከመሆኑም ባሻገር የምስጋናና የተስፋ በዓል ነው። በሕይወት፣ በጤና፣ በሰላም፣ በዝናብ፣ በፀሐይ፣ በሀብት፣ በልጅ፣ በከብት፣ በእህል፣ የባረከውንና አዕምሮና ምሪት የሰጠውን አምላካቸውን የሚያመሰግኑበት በዓል ነው።

በክረምቱ ወንዝ ሙላትና ጭቃ ለመገናኘት የተቆራረጡ ቤተሰቦች የሚገናኙበት፣ ገበሬው እና ቤተሰቦቹ በክረምቱ ዝናብ፣ ውርጭ፣ ደመና፣ ጤዛና ብርድ በብዙ ድካም እና ልፋት ከሚያርሱበት፣ ከሚያርሙበትና ከሚኮተኩቱበት ዕረፍት ማግኘታቸውን የሚያበስሩበት በዓል ነው። እንዲሁም እንስሳት በክረምቱ ዝናብና ጤዛ ኮቴያቸው ከሚነቀልበት፣ በተናዳፊው ዝንብ እና ወፍ አደጋ ነፃ የመውጣት ተስፋ የሚታይበት፣ ጽልመት መወገዱን ማብሰሪያና የብሩህ ተስፋ ምልክት ነው ይላሉ።



የዘንድሮው የያሆዴ በዓል በሆሳዕና ከተማ የያሆዴ ማክበሪያ "'ሀዲይ ነፋራ'' እጅግ በደመቀ መልኩ ተከብሯል፤

ተስፋ በጨለማ አሻግሮ ብርሃንን ማየት በመሆኑ ነጋችን ብሩህ እንዲሆን እንደ ቁስል ከሚመረቅዝ ምሬት፣ ከቂም በቀል፣ ከጥላቻ ወጥተን ይቅርታ ውስጥ ሆነን በንጹሕ ልብ የምንታረቅበት፣ ከስህተት የምንታረምበት፣ አንዱ ሌላኛውን የሚባርክበት፣ ክፉ በጋራ የሚረገምበት፣ ከዕምነት በሚመነጭ ተስፋ መሰናክሎችንና የሚያማርሩ ነገሮችን አልፈን ነፍሳችን የሚለመልምበት፣ የምንስተካከልበት፣ ጎዶሎ የሚሞላበት፣ ከትላንቱ ብቃት የተሻለ ዕውቀትና ብቃት በመፍጠር ለሥራ የሚነሳሳበት፣ የምንመራረቅበት፣ ሴቶችን፣ አረጋውያን፣ ወላጅ አጥ-ችግረኞችና አቅመ ደካሞች በክብር የሚደጋገፉበት የመተሳሰብ በዓል ነው።

አንዳንድ ሰዎች ያሆዴን ከመስቀል በዓል ለማያያዝ እንደሚሞክሩ የሚያነሱት አቶ ግርማ፣ ይህ ደግሞ ፈጽሞ ተዓማኒነት ያለው ማስረጃ ሊቀርብ የማይችልበት ሐሳብ ነው ይላሉ። ለዚህም በማረጋገጫነት የሚቀርበው ለያሆዴ በዓል ዝግጅት በሴቶች እንሰት፣ ቅቤ፣ ቆጮ፣ ምግብ ወዘተ ዝግጅት፤ በወንዶች የሰንጋ አደላለብ እና የዱቤ ግዥና ሽያጭ፣ የሳር ማከለል፤ በወጣቶች የሚካሄድ የእንጨት ዝግጅት፣ የወሮዬ ጨዋታ፣ ፊነጃ፣ ጋሚሻና ስንደዶ ለቀማ፤ በልጃገረዶች የሚከወኑ የቤት ውበት፣የቆጮ ዝግጅት፤ በልጆች የሚዘጋጅ ጦምቦራ፣ ኮንዳ ሥራዎች፣ የዋሸንት ጨዋታ፤ የመቻዕል ሜራ ግብይት ሥርዓት እንዲሁም ለምርቃት የሚዘጋጀው ጠሊላ፣ ማር፣ ወተት፣ ሰዳ፣ ቅቤ እና የምርቃት ሥርዓት አፈጻጸም፤ የይቅርታና የዕርቅ ሥርዓት፤ ያለው ለሌለው አካፍሎ ማክበር፣ ዘራሮ፣ ሳቴ፣የአተከና፣ የክትፎና ሌሎች የአመጋገብ ሥርዓት እና የያሆዴ የጨዋታዎች ሥርዓት፣ በአጠቃላይ በቅድመ ያሆዴ፣ በያሆዴ ዐውድ በድሕረ ያሆዴ የሚከወኑ ክዋኔዎች በመስቀል በዓል ወቅት በኦርቶዶክስ ዕምነት ተከታዮች ከሚከናወኑ ክዋኔዎች ጋር ፈጽሞ የማይገናኙ፣ በሀዲያ ባህላዊ ዕሴቶች ብቻ ተውቦ የቀረበ ባህላዊ በዓል ስለመሆኑ ማሳያዎች በመጥቀስ ያብራራሉ።

የዘንድሮ የያሆዴ በዓል በዞኑ ዋና ከተማ በሆሳዕና ከተማ ውስጥ በሚገኘው ያሆዴ ማክበሪያ "ሀዲይ ነፋራ" ከፌዴራል እና ከክልል እንዲሁም ከአጎራባች ዞኖች በርካታ እንግዶች በተገኙበት ከወትሮው እጅግ በደመቀ መልኩ ተከብሯል። በዓሉ ከዋዜማው ጀምሮ በደማቅ ሥነ ሥርዓት ተከብሯል።

በያሆዴ በዓል ሁሉም ሰው የየራሱ ድርሻ እንዳለው የጠቆሙት የባህልና ቱሪዝም ባለሙያዋ ወይዘሮ አለሚቱ ጋቦሬ እንደተናገሩት፤ በዓሉ ከመድረሱ አስቀድሞም ሁሉም ሰው የራሱን ድርሻ ለመወጣት ቅድመ ዝግጅት ያደርጋል፤ ከዚያ በኋላ ሁሉም በጋራ በደስታ በዓሉን ያከብራል፤ ፈጣሪውን ያመሰግናል ይላሉ።

ይህ የ"ያሆዴ" በዓል ሲነሳ ሁሌም አብሮ የሚነሳው ወጣት ወንዶች በአካባቢያቸው ተሰብስበው በየቤቱ እየተዘዋወሩ ምሽቱን ሙሉ የሚጨፍሩት የያ ሆዴ ጭፈራ (ጨዋታ) ባሕላዊ ጨዋታ ነው። በዚህ ዕለት ማታ ፉሊታ ( ያሆዴ) የሚጨፈርበትና ጨፋሪዎች ደግሞ "ከዚህ ቤት ችጋር ይውጣ፣ በሽታ ይውጣ!" ብለው ችቦ እያቀጣጠሉ ይጨፍራሉ። ጨፋሪዎች መርቀው ሲወጡ የቤቱ አባወራና እማወራ እናንተም እደጉ በማለት ይመርቁና ይሸኟቸዋል።

ወይዘሮ አለሚቱ ጋቦሬ እንደሚሉት፤ የያሆዴ እለት ሁሉም የሀዲያ ሕዝብ የሚመራረቅበት ነው። ያሆዴ ጭፈራን ከሌሎች ጭፈራዎች የተለየ የሚያደርገው ልጆች ወላጆቻቸውን የሚመርቁበት በመሆኑ ነው። በየገቡበት ቤት ሁሉ አተካና እና ለበዓሉ ተብሎ የተዘጋጁ ምግቦችን እየበሉ የቤቱን አባወራና እማወራ ይመርቃሉ።

ለዚህ በዓል ሴቶችም ከአለባበስ እስከ ፀጉር አሠራር ድረስ በተስተካከለ ሁኔታ ይዘጋጃሉ። የሀገር ሽማግሌዎች ተሰልፈው ሥርዓቱን ያስጀምራሉ፤ ይከታተላሉ፤ ይመርቃሉ።

የሀዲያ ብሔር እሴት የሆነው ያሆዴ ከነሐሴ ወር ጀምሮ በብሩህ ተስፋ የተሞላ ነው። በዚህ በዓል ሴቶች ቀደም ብለው ሥራቸውን ይጀምራሉ። ቤታቸውን ያዘጋጃሉ። በኅብረት ይሠራሉ። ወንዶች ደግሞ እንጨት ያዘጋጃሉ። ሰንጋ ይገዛሉ። ሕፃናት ጦምቦራ (ችቦ) ቀድመው ይሠራሉ።

በሀዲይ ነፈራ በተካሄደው የያሆዴ የአከባበር ሥርዓት ላይ ንግግር ያደረጉት የሀዲያ ዞን ዋና አስተዳደር አቶ አብርሃም መጫ እንደተናገሩት፤ በያሆዴ ሰው ብቻ ሳይሆን ከብቶችም አዲስ ዓመት የሚቀይሩበት በመሆኑ ከአምስት ወር ጀምሮ ጥብቅ ወይም ክልክል ሳር ይፈቀድላቸዋል።

ያሆዴ ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተሸጋገረ ለዛሬ የደረሰ ባህላዊ እሴት መሆኑን ጠቅሰው፣ የዘንድሮውን የያሆዴ በዓል ከወትሮው የሚለየው ኢትዮጵያ የበርካታ ድሎች ባለቤት በሆነችበት ወቅት መከበሩ መሆኑ ነው ይላሉ:: በተለይም ባለፉት ዓመታት በዓሉ በድምቀት እንዳይከበር እንቅፋት ሆኖ የነበረው ኮቪድ 19 ስጋት በቀነሰበት እና ሌሎች ሀገራዊ ድሎች በተመዘገቡበት ማግስት መከበሩ ለየት እንደሚያደርገው ጠቁመዋል።

ያሆዴ የሀዲያ ብሔር ዘመን መለወጫ በዓል የተጣሉ የሚታረቁበት፣ የተቸገሩ ወገኖች የሚደገፉበትና በአንድነት የሚከበር ታላቅ ሕዝባዊ በዓል ነው ያሉት አቶ አብርሃም፤ በዓሉን በዓለም ቅርስነት በዩኒስኮ ለማስመዝገብና ባህላዊ ይዘቱን ጠብቆ ለቀጣይ ትውልድ ለማስተላለፍ በትኩረት እየተሠራ እንደሆነም አቶ አብርሃም ገልፀዋል::

ኢትዮጵያ ካሏት እምቅ እና ከትውልድ እስከ ትውልድ ተሻጋሪ እሴቶች አንዱ ያሆዴ በዓል ነው ያሉት ደግሞ የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ምክር ቤት ዋና አፈ ጉባኤ ወ/ሮ ፋጤ ሲርሞሎ ናቸው:: ያሆዴ የተጣላ ታርቆ፣ ያለው ለሌለው አካፍሎ፣ በመተሳሰብ እና በፍቅር መጪውን አዲስ ዓመት በደስታ የሚቀበልበት ልዩ የሀዲያ ሕዝብ መገለጫ መሆኑን አስታውቀዋል።

አስታራቂዎችም ቂም ይዞ አዲስ ዓመትን መቀበል አይቻልም በማለት የተጣሉ ሰዎችን የሚያስታርቁበት መሆኑን በማንሳት የሰላምና የእርቅ ጉዳይ ሲነሳ ያሆዴን አለማንሳት አይቻልም ሲሉ ዋና አፈ-ጉባኤዋ ተናግረዋል። እነዚህን መልካም እሴቶችን አቅፎ የያዘው የያሆዴ በዓል ለቀጣይ ትውልድ እንዲተላለፍ ጥረት ይደረጋልም ብለዋል:: የሀዲያ ብሔር ዘመን መለወጫ የሆነውን ያሆዴ በዓልን በጥናትና ምርምር ሥራዎች በማስደገፍ የመጠበቅና የማልማት ሥራ ትኩረት ሊሰጠው እንደሚገባም ወ/ሮ ፋጤ ሲርሞሎ አሳስበዋል::

በበዓሉ አከባበር ሥነ-ሥርዓት ላይ ተገኝተው የእንኳን አደረሳችሁ መልዕክት ያስተላለፉት የባህልና ስፖርት ሚኒስትር አቶ ቀጄላ መርዳሳ በበኩላቸው፤ የሀዲያ ሕዝብ እንደ አንድ ማኅበረሰብ መኖር የጀመረው ከሺህ ዓመታት አንስቶ መሆኑን እና በመካከለኛው ክፍለ ዘመን የሀዲያ መንግሥት እና ማኅበረሰብ ጠንካራ አደረጃጀት እንደነበረውም ታሪክ ይነግረናል ብለዋል።

የሀዲያ ሕዝብ በፖለቲካ ማኅበር ተደራጅቶ ሲንቀሳቀስ የነበረ ራሱን የቻለ ጠንካራ እና ታላቅ ሕዝብ እንደሆነ ያወሱት ሚኒስትሩ፤ የሀዲያ የዘመን መለወጫ በዓል የሆነው (ያሆዴ) የሀዲያ ሕዝብ የጥንታዊ ሥልጣኔ መገለጫ መሆኑን አስታውቀዋል።

አንዳንዶች የያሆዴ በዓልን ከመስቀል ጋር ያያይዙታል ያሉት አቶ ቀጄላ፣ ነገር ግን በዓሉ ሃይማኖታዊ እንዳልሆነ እና የሀዲያ ሕዝብ የፈጠረው ታሪካዊ ቅርስ እና ጥንታዊ የሥልጣኔ መገለጫ መሆኑን ጠቅሰዋል። እንደዚህ ዓይነት በዓላት መቀጠል እና ለትውልድ መተላለፍ ያለባቸው መሆኑንም በመልዕክታቸው ያነሱት ሚኒስትሩ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤታቸው በዚህ ረገድ አስፈላጊውን እገዛ እንደሚያደርግም ጠቁመዋል።

# ሳምንቱን በታሪክ

# ንግሥት ዘውዲቱ

ተገኝ ብሩ



የታሪክ ሰነዶችን አገላብጠን፤ ከወቅት ጋር አሰናኝተን በትውስታ ያለፈን ማሳየታችንን ቀጠልን። ዛሬም በሳምንቱ ውስጥ ኢትዮጵያ ላይ ሆነው ካለፉ ዓበይት ታሪካዊ ሁነቶች ውስጥ አንዱን መርጠን ወደናንተ ለማድረስ ብዕራችን አነሳን። በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ቀዳሚ ሴት መሪ በመሆን ይታወቃሉ። 14 ዓመታት ኢትዮጵያን ንግሥት ሆነው መርተዋል።

ሴቶች በአመራርነት ላይ ቢሳተፉ ብቁ መሆናቸውን በነገሡበት ዘመን በሠሩት ሥራ አሳይተዋል። በአገሪቱ አዳዲስ ሕጎችን በማውጣትና በመተግበር ሕግና ሥርዓት ተግባራዊ እንዲሆን ጥረዋል። ሀገራቸውን በዓለማቀፍ ደረጃ እውቅና እንድታተርፍና ተሳትፎዋ ከፍ እንዲልም ሠርተዋል። እኚህ ንግሥት ወደ ንግሥናው የመጡት መስከረም 21 ቀን 1909 ዓ.ም ነበር። ቆራጥና ብርቱዋ ንግሥት ዘውዲቱን በዛሬ ገፃችን ልንዘክር ወደናል።

የተለያ ድረ ገፆችን፣ የኢትዮጵያ ታሪክ እና የ20ኛ ክፍለ ዘመን ኢትዮጵያ ፤ በጥላሁን ብርሀነ ሥላሴ መጽሐፍትን በዋቢነት ተጠቅመናል።

እነዋሪ ከተማ ሰገነት የተባለች መንደር ተወልደው እትብታቸው የተቀበረበት ነው። ቅዳሜ ሚያዚያ 22 ቀን 1868 ዓ.ም ደግሞ ወደዚህች ምድር የተቀላቀሉበት። አባታቸው ዳግማዊ ምኒሊክ በወቅቱ የሸዋ ንጉሥ ነበሩ። በኋላም ኢትዮጵያን በንጉሠ ነገሥትነት መርተዋል። እናታቸው ወይዘሮ አብቸው ጠንካራና ቆራጥ ሴት እንደነበሩ ይነገራል። ንግሥት ዘውዲቱ ለአባታቸው ዳግማዊ ምኒሊክ ሦስተኛ ልጅ ሲሆኑ ከልጅ ኢያሱ ቀጥለው መኳንንትና ሕዝቡ መክሮና ዘክሮ በምርጫ በኢትዮጵያ ዙፋን ላይ የተቀመጡ ብቸኛ ንግሥትም ናቸው።

የንጉሥ ልጅ እንደመሆናቸው እድገታቸው በድሎት ነበር። በእርግጥ ገና ጉልበታቸው ሳይጠና ነበር ያገቡት። በወቅቱ ሸዋን ያስተዳድሩ የነበሩት አባቷ ዳግማዊ ምኒሊክ ከትግራይ ገዢው አፄ ዮሐንስ 4ኛ ጋር ባለመግባባት ግጭት ውስጥ በተደጋጋሚ ይገቡ ነበር። ኋላ ላይ ሁለቱ ነገሥታት ባደረጉት ስምምነት መሠረት መግባባት ላይ ደረሱ። ግንኙነታቸውንም ለማጠንከር እንዲረዳቸው አፄ ዮሐንስ አፄ ምኒሊክን ይበልጥ ግንኙነታችን ይጠነክር ዘንድ ሴት ልጅዎትን ለወንዱ ልጄ አርዓያ ሣሕለ ሥላሴ ስጡኝ ብለው ጠየቁ።

ለዚህም አፄ ዮሐንስ ራስ ገብረኪዳን፣ ራስ አሉላ እና ቢትወደድ ገብረ መስቀልን በሽምግልና ወደ አፄ ምኒሊክ ላኩ። ዳግማዊ ምኒሊክም ልጃቸው ዘውዲቱን ከአፄ ዮሐንስ ልጅ ጋር ማጋባት ፈቀዱ። በዚህም ንግሥት ዘውዲቱ የስድስት ዓመት ሕጻን ሳሉ ለ12 ዓመቱ የአፄ ዮሐንስ ልጅ አርአያ ሥላሴ ዳሩዋቸው። ከሽምግልናው በኋላ ወዲያው ድግስ ማሰናዳትና ለሠርጉ የሚሆን መሰናዶ ማድረግ ተጀመረ።

ጋብቻቸውም እጅግ በደመቀ ሁኔታ በተክሊልና በቁርባን ተፈጸመ። በዚያን ወቅት የሁለቱ ነገሥታት ልጅ እንደመሆናቸው የሠርጉም ማማርና የሽልማቱ ብዛት የተለየ እንደነበር የታሪክ ድርሳናት ይጠቅሳሉ።

ነገር ግን የንግሥት ዘውዲቱና የአፄ ዮሐንስ ልጅ አርአያሥላሴ ጋብቻ የዘለቀው አርዓያሥላሴ እስከ አረፉበት 1880 ዓ.ም ብቻ ነበር። መቀሌ ላይ ሕይወታቸው ያረፈው የንግስት ዘውዲቱ ባል አርዓያሥላሴ የንጉሥ አፄ ዮሐንስ ቤተ መንግሥት ኀዘን አለበሰው። ከጊዜ በኋላም ደርቡሾች በመተማ በኩል ወደ ኢትዮጵያ መግባታቸውን የሰሙት አፄ ዮሐንስ ለመዋጋት ወደ በጌ ምድር ጦራቸውን ይዘው ዘመቱ። ንግሥት ዘውዲቱም አብረው ዘመቱ።

ከዚያ ጦርነት በኋላ አፄ ዮሐንስና ንጉስ ምኒሊክ በተደጋጋሚ በመካከላቸው ቅሬታ እየተፈጠረ ይወቃቀሱ ነበር። በዚህም አፄ ዮሐንስ የአፄ ምኒሊክ ልጅ የሆነችውን ንግስት ዘውዲቱን በጎሐ ጽዮን በኩል ወደ አባታቸው ላኳቸው።

ከዚያ በኋላ ንግሥት ዘውዲቱ ከደጃዝማች ጓንጉል ዘገየ ጋር ተጋብተው አንድ ልጅ ወልደዋል። ልጅቷ ብዙም ሳትይቆይ በ2 ዓመቷ አርፋለች። ከደጃዝማች ጓንጉል ጋር ያደረጉት ጋብቻም ሳይፀና ቀርቶ ተፋተዋል። ቀጥሎም ከደጃዝማች ውቤ አጥናፍሰገድ ጋር ተጋቡ፤ ነገር ግን ከ4 ዓመት በላይ ሳይቆዩ ተፋቱ። መልሰው ከደጃዝማች ጉግሳ ወሌ ጋር ተጋቡ። ደጃዝማች ጉግሳ ወሌ በወቅቱ በጌምድርን ያስተዳድሩ ነበር።

ነገር ግን ንግሥት ዘውዲቱ ወደ አዲስ አበባ የሚመልሳቸው አንድ ጉዳይ ተፈጠረ። አባታቸው አፄ ምኒሊክ በፀና መታመማቸውን ሰሙ። ዳግማዊ አጼ ምኒሊክ በ1901 ዓ.ም በታመሙ ጊዜ ንግሥት ዘውዲቱ ከደብረታቦር ወደ አዲስ አበባ በመምጣት አባታቸውን ከእቴጌ ጣይቱ ጋር በመሆን ማስታመም ጀመሩ። ለተከታታይ 6 ዓመታት ያስታመሟቸው አባታቸው በ1906 ዓ.ም መሞታቸውን ተከትሎ እጅጉን ኀዘን ዋጣቸው።

በኋላም ልጅ ኢያሱ እቴጌ ጣይቱና ንግሥት ዘውዲቱ ከቤተ መንግሥት እንዲወጡ ባልታወቀ ምክንያት ባዘዙ ጊዜ ከቤተ መንግሥት ለመውጣት ተገደዱ። ፋሌ ወደሚገኘው እርስታቸው ሄደው ተቀመጡ። ልጅ ኢያሱም ንግስት ዘውዲቱን ከሌላ ሰው ጋር ሊያጋቧቸው ብዙ ቢጥሩም በቁርባን ያገባሁት ጉግሳ ወሌ እያለ ሌላ አላገባም በማለታቸው፤ ባላቸው ከበጌ ምድር እንዲመጡና አብረው እንዲኖሩ አደረጉ።

በዚህ ሁኔታ ፋሌ ላይ የቆዩት ንግሥት ዘውዲቱ ወደ ስልጣን የሚመጡበት ጉዳይ ተከሰተ። እርሱም ልጅ ኢያሱ መስከረም 17 ቀን 1909 ዓ.ም ከስልጣን እንዲወርዱ ተፈረደባቸው። ልጅ ኢያሱ ከንግሥና ስልጣን ሲወርዱ፤ መኳንንቱና ሕዝቡ ስልጣን ለማን ይገባል በማለት መክሮና ዘክሮ አንድ ውሳኔ አሳለፈ። ዘውዲቱን ግርማዊት ንግሥተ ነገሥት፣ ራስ ተፈሪ መኮንንን አልጋ ወራሽ እና ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ እንዲሆኑ ወስነው፤ መስከረም 21 ቀን 1909 ዓ.ም ዘውዲቱ "ንግሥተ ነገሥት ዘኢትዮጵያ" ተብለው ነገሡ።

በመኳንንቱ ምክር መሠረት ጳጳሱና እጨጌ ወልደጊዮርጊስ "ኢያሱን የተከተልክ፣ ያነገሥናትን ዘውዲቱንና ራስ ተፈሪን የከዳህ፣ ውግዝ ከመአርዮስ" እያሉ በአዋጅ አወገዙ። ከዚህ በኋላ የጥቅምቱ የሰገሌ ጦርነት ተደረገ፤ ከጦርነቱ በኋላ የዘውድ በዓሉ የካቲት 4 ቀን 1909 ዓ.ም እንዲሆን ታዘዞ፣ ለዘውዱ በዓል በኢትዮጵያ አዋሳኝ ያሉት የእንግሊዝ ሱዳንና የእንግሊዝ ሱማሌ ገዥዎች፤ የፈረንሳይ ሱማሌ ገዥ እና በኢትዮጵያም ታላላቅ ራሶች እንዲሁም የየአውራጃው ገዥዎች በተገኙበት በዕለተ እሑድ አባታቸው ባሠሩት በትልቁ ደብር በመናገሻ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን በሊቀ ጳጳሱ በአቡነ ማቴዎስ እጅ ቅብዐ መንግስት ተቀብተው የንጉሠ ነገሥቱን ዘውድ ጫኑ።

ከዚህም በኋላ እንደ ሥርዓተ ንግሡ ሕግ፤ ንግሥተ ነገሥት ዘውዲቱ በአባታቸው ዙፋን ተቀምጠው መንገሣቸውን፤ ደጃዝማች ተፈሪም ራስ ተብለው አልጋ ወራሽና ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ መሆናቸውን በቤተ ክርስቲያኑ ቅጥር ግቢ በተሰበሰበው ሕዝብ ፊት አዋጅ ተነገረ።

**ንግሦተ ነገሥት ዘውዲቱ በስልጣን ዘመናቸው የፈጸሙት ዓበይት ተግባራት**

የኢትዮጵያን የዓለም መንግሥታት ማኅበር(ሊግ ኦፍ ኔሽን) አባልነት ማድረጋቸው ተጠቃሹ ነው። ንግሥቲቱ በስልጣን ላይ ሳሉ፤ የዓለም መንግሥታት ማኅበር (ሊግ ኦፍ ኔሽንስ) ጠቅላላው ጉባዔ በፈረንጅ አቆጣጠር መስከረም 28 ቀን 1923 ወይም በኢትዮጵያ አቆጣጠር መስከረም 17 ቀን 1916 ዓ.ም. ባደረገው ስብሰባ ኢትዮጵያ አባል እንድትሆን ፈቃዱ መሆኑን ያሳወቁበት ጊዜ ነበር።

በዚያን ወቅት የኢትዮጵያው መልዕክተኛ ደጃዝማች ናደው አባልነቱ ለኢትዮጵያ መፈቀዱን በማስመልከት ከፍ ባለ ደስታ ስሜት የሚከተለውን ታሪካዊ ንግግር አድርገውም ነበር።

**" ክቡራን ሆይ!**

**ጠቅላላው ጉባኤ በበጎ ፈቃደኝነትና በትክክለኛ ፈራጅነት፣ በጥልቅ አስተሳሰብ መርምሮ ወደ ማኅበሩ ስለመግባት ያቀረብነውን ጥያቄ ስለ ተቀበለው፣ የኢትዮጵያ መልዕክተኞች በግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና በልዑል ራስ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ስም፣ እንዲሁም በመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ስም ምስጋና ያቀርባሉ።**

**የሰውን ልጅ ወንድማማችነት የመመሥረት ዓላማ ባለው ውሳኔያችሁ የተሰማንንም ልባዊ ደስታ እንድገልጽላችሁ ይፈቀድልኝ ዘንድ እለምናለሁ። ኢትዮጵያ ባለፈው የጀግንነት ታሪክና በከፍተኛ ሥልጣኔዋ የምትኮራ ሀገር መሆንዋ፣ የዘመናዊ ድርጅቶች ከሚያስገኙላትም ፍሬ ተካፋይ ለመሆን ብርቱ ጥረትና ሙሉ ፈቃደኛነት እንዳሳት የታወቀ ነው።**

**መንግሥታችንም ይህን ጥረት ወደ መልካም ግብ ለማድረስ የዓለም መንግሥታትን አንድነትና ኅብረት የሚያስፈልግ መሆኑን በጥብቅ ያምንበታል።"**

በማለት መልዕክታቸውን አስተላልፈው ነበር። በዚህም ንግስት ዘውዲቱ ለኢትዮጵያ ዓለማቀፍ ግንኙነት ጠንካራ መሠረት የጣሉ የአገር ባለውለታ መሆናቸውን ብዙዎች ያነሳሉ።

**የባሮች ነፃነት ደንብ ማውጣት**

ይህ ደንብ ምንም እንኳን በወቅቱ በመኳንንቱ ባይወደድም ባሮችን ነፃ የሚያወጣና በአንፃራዊነትም ፍትሕ የሚያሰፍን ስለነበር በብዙዎች የተወደሰ ነበር። በልዑል አልጋ ወራሽ ራስ ተፈሪ መኮንን መጋቢት 16 ቀን 1916 ዓ.ም በግርማዊት ንግሥት ዘውዲቱ ፈቃድ ስለ ባሮች ነፃነት የወጣው ደንብ «ስለ ባሮች አስተዳደርና ነፃነት የቆመ ደንብ» የሚል ርዕስ ነበረው።

ይህ አብዛኛውን ኅብረተሰብ አስደስቶ የነበረ ደንብ እንደ መጽሐፍ ሆኖ በልዑል አልጋ ወራሽ ማተሚያ ቤት ታትሞ ወጥቶ ነበር። መጽሐፉ ባለ 10 ገጽ ሲሆን የደንቡ ቃል በ45 ቁጥሮች ተመድቦ የተለያዩ ውሳኔዎችንና ደንቦችን ይዞ ነበር።

በወቅቱ በወጣው ደንብ ምክንያት አንዳንድ መኳንንትና ባለብዙ ባሮች የሆኑት አንዳንድ ሰዎች በልባቸው ቅሬታ ገብቶ አዘኑ። ከዚያም ውስጥ የጦር ሚኒስትሩ ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ አንዱ ነበሩ።

**የአፄ ቴዎድሮስ ዘውድ ማስመለስ**

በቀደሙት ዓመታት ወደ እንግሊዝ ተዘርፎ የነበረውን የአፄ ቴዎድሮስ ዘውድ የማስመለሱን ሥራ የሠሩትና ያስተባበሩት ንግስት ዘውዲቱ ነበሩ። በብዙ ጥረት ከእንግሊዝ አገር የመጣው የአፄ ቴዎድሮስ ዘውድ ሐምሌ 4 ቀን 1917 ዓ.ም ቅዳሜ ለግርማዊት ንግሥት ዘውዲቱ ተመልሷል።

ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ በነገሡ በ13 ዓመት ተኩል ረቡዕ መጋቢት 24 ቀን 1922 ዓ.ም በ10 ሰዓት አረፉ። የሞታቸው ዜና እንደተሰማም በከተማው የኀዘን ጥላ አጠላበት። አባታቸው ዐፄ ምኒልክ በተቀበሩበት በታዕካ ነገሥት በዓታ ቤተ ክርስቲያን ተቀበሩ።

# የዝነኞች ገጽ

## የዜማ አባት - ማዲንጎ አፈወርቅ
(1970 - 2015 ዓም)

አቤል ገ/ኪዳን

የትውልድ ስፍራው ጎንደር አዘዞ ነው። ወቅቱም ሚያዝያ 10 ቀን 1970 ዓም። ወይዘሮ ሀገርነሽ ዋሴ እና አቶ አፈወርቅ መንግሥቱ ወንድ ልጅ ወለዱ። ስሙንም ተገኔ አሉት፤ "ጠበቃዬ ፥ ጋሻ መከታዬ ማለት ነው። ልጃቸውን በወለዱ በሦስተኛው ወር ግን የልጃቸው እትብት የተቀበረባትን አዘዞን ትተው ወደ ትውልድ ቦታቸው ደብረ ታቦር ሄዱ። ይህ ልጅ በኋለኛው ዘመን በኢትዮጵያ ሙዚቃ የሚጠቀስ ስም ካፈሩ ድምጻውያን መካከል አንዱ የሆነው ማዲንጎ አፈወርቅ ነው።

የማዲንጎ ቤተሰብ ለመንፈሳዊ ዓለም ቅርብ ነው። አባቱን ጨምሮ አብዛኛው ቤተሰቡ የቤተ ክህነት አገልጋይ ነበሩ። ምናልባትም የዜማ ተሰጥዖው ከዚያው የመነጨ ሳይሆን አይቀርም። በልጅነቱ የሙዚቃ ፍቅር እንዳደረበት እና ገና በ9 ዓመቱ በቀበሌ ኪነት ውስጥ ማይክ እንደጨበጠ ይናገር የነበረው ማዲንጎ፥ የሰባተኛ ክፍለ ጦር የ603 ኮር የሙዚቃ ቡድን ልምምድ ሲያደርግ ከተመለከተ በኋላ ግን ልቡ ሙዚቀኛ ለመሆን ቆረጠ። ድምፃዊ መሆን እችላለሁ በማለት እድል እንዲሰጡት ጠየቀ። እናም በወቅቱ እድሉን አግኝቶ የድምፃዊ ኤፍሬም ታምሩን " ና ተላክ ልቤ ፥ ልላክህ ልስደድህ ልቤ" የተሰኘውን ሙዚቃ ተጫውቶ አድናቆት ተቸረው። ተቀባይነትን አግኝቶም በዛው በወታደር ቤት ሙዚቃውን የቀጠለ ሲሆን፥ "ማዲንጎ" የሚለው ስሙም የወጣለት እዚያው ነው።

ማዲንጎ ከጦሩ ከወጣ በኃላ በ1982 ዓም አካባቢ ገና በ12 ዓመቱ በባህር ዳር የሙዚቃ ሥራዎችን በማቅረብ አንድም ድምፃዊ የመሆን ሕልሙን መስመር ያስያዘበት በሌላ በኩል ገቢ በማግኘት እራሱንና ቤተሰቦቹን ማገዝ የቻለበትን ሁኔታ መፍጠር ችሏል። በወቅቱ 120 ብር ይከፈለው ነበር። በመቀጠልም ወደ አዲስ አበባ ከተማ በመምጣት እርጎዬዎችን እና ላፎንቴኖችን ጨምሮ የተለያዩ የሙዚቃ ባንዶችን በመቀላቀል የታዋቂ ሙዚቀኛ ስራዎችን በማቀንቀን ተወዳጅነትን አገኘ።

በ1991 "ስያሜ አጣሁላት" የተሰኘውን እና እሱ የልጅነቴና ከሰው ጋር አስተዋወቀኝ የሚለውን አልበሙን ለሕዝብ ጆሮ አደረሰ። ከጥቂት ዓመታት በፊት ከአዲስ አድማስ ጋዜጣ ጋር ባደረገው ቃለ መጠይቅ ስለ መጀመሪያ አልበሙ እንዲህ ብሎ ነበር "የመጀመሪያው አልበሜ የልጅነት ሥራዬ ነው። ያኔ ጠቆር ያልኩ ነበርኩኝ፤ እንዳሁኑ አልገፈፍኩም ነበር። አሁን እንደ እባብ ቆዳ ቀይሬያለሁ። የሆነ ሆኖ 'ስያሜ አጣሁላት' በልጅነት ዕድሜ ከሕዝብ ያገናኘኝ ሥራ ነው። ወቅቱ የኢትዮ ኤርትራ ጦርነት ነበር። ታዲያ 'ስያሜ አጣሁላት' እና 'አማን ነው ወይ ጎራው' የተሰኙት ሁለት ዘፈኖች በተለየ መልኩ ተወደውልኝ ነበር።"ይላል።

በዚህም አድናቆትን እና የሕዝብ ፍቅርን ሲያገኝ ከዓመታት በኋላ በ1997 "አይደረግም" የተሰኘውን ሁለተኛ አልበሙን ለሕዝብ በማድረስ ተወዳጅነቱን ከፍ አደረገ። ይህ አልበሙም አይደረግም፣ የአፋሯ ቆንጆ፣ ሰው የለኝም፣ ማህሌት፣ ሞኙ ልቤ እና ሌሎች ተወዳጅ ዜማዎችን ያካተተ ነው። በተለይም በዚህ አልበሙ ላይ የተጫወተው የአራት ታላላቅ ድምፃውያንን የትዝታ ዜማ አንድ ላይ ያዋሀደው ትዝታ የማዲንጎን የመዝፈን ችሎታ በሚገባ ያሳየ ነበር።

ከዚያም "አይደረግም" የተሰኘውን ሁለተኛውን አልበሙን ካወጣ ከስምንት ዓመት በኋላ "ስወድላት" የተሰኘውን ሦስተኛ አልበሙን በ2007 ዓ.ም ለአድማጮቹ እንካችሁ አለ። በዚህ የሙዚቃ አልበሙ ውስጥ ላላተርፍ፣ ስወድላት፣ አቅሜን፣ አይሆንልኝም፣ እባክሽ ታረቂኝ፣ ከተለያየን ፣ ውሰጃት፣ ዳኛ፣ ጎዳናው፣ ማተቧ፣ ማርማር የተሰኙና ሌሎች ሙዚቃዎች ተካተዋል። በስወድላት አልበምም በተለያዩ የሙዚቃ ውድድሮች እጩ እንዲሁም "ምርጥ የፍቅር አልበም" ተብሎ ለመሸለም ችሏል።

እንዲሁም ከአልበሞቹ በተጨማሪ "በላይ"፣ ከብርሃኑ ተዘራ ጋር የተጫወተው "ሰላም ያገር ሰው"፣ ለ"ዓባይ ወይስ ቬጋስ" ፊልም የሰራው ማጀቢያ ሙዚቃ ከሥራዎቹ ውስጥ ግንባር ቀደም ሆነው ይጠቀሳሉ። "በማንኛውም ሙያ ውስጥ ያላችሁ ወጣቶች፥ በጥረት እንጂ ከመሬት ተነስቶ የሚመጣ ነገር የለም፤ በድንገት የሚመጣ ነገርም ጠቃሚ አይደለም" በማለት ያስተላለፈው መልዕክትም የሚታወስ ነው።



አርቲስት ማዲንጎ አራተኛ አልበሙን ለአድማጮች ለማድረስ በመሥራት ላይ እንደነበርም ነው የተሰማው። አይቀሬው ሞት ድንገት ፈጥኖ ቀደመው እንጂ። ከሶስተኛው አልበም መውጣት በኋላ ከሰይፉ ፋንታሁን ጋር ባደረገው ቆይታ በቀጣይ በስምንት ዓመታት ውስጥ ሶስት አልበሞችን ለማውጣት አቅዶ እንደነበር የተናገረው አርቲስት ማዲንጎ አፈወርቅ በወጣትነቱ እና ብዙ መሥራት በሚችልበት ዕድሜው ባደረበት ድንገተኛ ሕመም ምክንያት መስከረም 17 ቀን 2015 ዓም ከዚህ ዓለም በሞት ተለየ። ከወይዘሮ ሮዛ ይግዛው ጋር በነበረው ትዳርም ዲቦራ የተሰኘች ሴት ልጅ አፍርቷል።

ማዲንጎ በማኅበራዊ ሕይወቱ እና በበጎ አድራጎት ሥራው ተጠቃሽ ነው። ስለ በጎ ሥራው ከሚመሰክሩ ሰዎች መካከል አንዱ አርቲስት አለልኝ መኳንንት ጽጌ ነው። አለልኝ እንዲህ ይላል "መጽሔተ ጥበብ" የሬድዮ ፕሮግራማችን ላይ የተቸገሩ፣ በክፉ ደዌ ተይዘው መታከሚያ ያጡ፣ ሰው መሐል ሆነው ሰው የራባቸው እና የሰው ያለህ የሚሉ ሰዎችን አድማጮቻችንን በማስተባበር የምንረዳበት"የፍቅር ቃል" በተሰኘው ዝግጅት ላይ ስማቸው እንዳይጠቀስ አደራ ብለው ከሚረዱ ከሚደግፉ በጎ አድራጊዎች አንዱ ወንድሜ ማዲንጎ አፈወርቅ ነበር" ብሏል።

በዘንድሮው የበጎ ሰው ሽልማት መርሐ ግብር ላይም በበጎ አድራጎት ሥራ የተሸለመው ወጣት ሄኖክ ፈቃዱም እንዲሁ ለዚህ በጎነቱ ምስክር ነው። "ከአምስት ዓመት በፊት በአንድ ማለዳ ለአርቲስት ማዲንጎ አፈወርቅ ስልክ ደወልንለትና ለባይሽ ኮልፌ በጎ አድራጎት ብቸኛ እናቶቻችን አስቤዛ ለመግዛትና ለበዓል እንዲሆን ጫማ መጥረግ ፕሮግራም አለንና እባክህ ተገኝ አልነው፤ 'ኮንሰርት አለኝ ዛሬ ወደ አሜሪካ እበራለሁ፣ ይህ በረከት ከሚያልፈኝ ለምን አሁን መጥቼ እኔ ጫማ አልጠርግም' አለን። እንዳለውም ጓደኛችን አብርሽ ያለበት ቦታ በአምስት ደቂቃ ውስጥ ደርሶ ዝቅ ብሎ ጫማ በመጥረግ ሌሎች የምንወዳቸው ደጋጎች እንዲሳተፉ መነሳሳትን ፈጥሮልናል" በማለት ያስታውሳል። ለሙያ አጋሮቹ ድጋፍ በማድረግም ማዲንጎን የሚቀድመው ማንም እንደሌለ ብዙ አርቲስቶች ምስክርነታቸውን ሰጥተዋል።

ማዲንጎ ሀገር ወዳድ አርበኛም ነው። በተለይም ኢትዮጵያ በተፈተነችበት ወቅት እያመመው ግንባር ድረስ በመሄድና በማሰልጠኛ የሚገኙ ምልምል ወታደሮችን በማነቃቃት የራሱን ታሪክ የሠራ ብርቅዬ አርቲስት ነበር። ግንባር ድረስ በመዝመትም ማዲንጎ አፈወርቅ በወርቃማ ድምጹ አገር ወዳድ ወጣቶችን ሳይሰስት አዝናንቷል። ለዚህም በቅርቡ ከጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ እጅ እውቅና እና ሽልማት ተበርክቶለታል።

የማዲንጎ ዜና ዕረፍት ከተነገረ በኋላም ብዙዎች የተሰማቸውን ኃዘን በማኅበራዊ ሚዲያ ገጻቸው ገልጸዋል። ፕሬዚዳንት ሣሕለወርቅ በማኅበራዊ ትስስር ገጻቸው ባሰፈሩት መልዕክት ፥ "ታዋቂው ድምጻዊ ማዲንጎ አፈወርቅ ገና በአፍላ ዕድሜ ላይ እያለ ከዚህ ዓለም በሞት በመለየቱ በጣም አዝኛለሁ። ለቤተሰቡ፣ ለወዳጅ ዘመዶቹና ለአድናቂዎቹ መጽናናትን ብርታትን እመኛለሁ" ብለዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ በበኩላቸው ባስተላለፉት የኃዘን መልእክት "አርቲስት ማዲንጎ አፈወርቅ በማረፉ የተሰማኝ ኀዘን ከባድ ነው። ለሀገሩ በአጭር እድሜው ብዙ የሠራ ከያኒ ነው። ሀገር በተደፈረች ጊዜ ሕመሙን እየቻለ ግንባር ተገኝቶ ሠራዊቱን አጀግኗል። ሠልጣኞችን አበርትቷል። ነፍሱ በሰላም ትረፍ።"ብለዋል።

የመከላከያ ሚኒስትር አብርሃም በላይ፣ የኢንዱስትሪ ሚኒስትር መላኩ አለበል፣ የማዕድን ሚኒስትር ታከለ ኡማ፣ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ርዕሰ መስተዳድር ይልቃል ከፋለ፣ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ አዳነች አቤቤ እና የብሔራዊ መረጃና ደኅንነት አገልግሎት ዳይሬክተር ጀነራል ተመስገን ጥሩነህ በአርቲስት ማዲንጎ አፈወርቅ ሕልፈተ ሕይወት የተሰማቸውን ኃዘን በማህበራዊ ትስስር ገጻቸው ገልጸዋል። በአዲስ አበባ የሚገኘው የሩሲያ ኤምባሲም ኃዘናቸውን ከገለጹት መሀከል ተጠቃሽ ነው።

የሙያ አጋሮቹ በበኩላቸው ባስተላለፉት መልዕክት በወዳጃቸው ሞት ልባቸው መሰበሩን ገልጸዋል። ከእነዚህም መካከል ድምጻዊት ሐመልማል አባተ ባስተላለፈችው መልዕክት "በሰማሁት ነገር እጅግ ደንግጫለሁ። ያለ እድሜህ ቀድመህ ብትሄድም አንረሳህም። ጓደኛዬ ነፍስህ በሰላም ትረፍ" በማለት ኃዘኗን ስትገልጽ ጎሳዬ ተስፋዬ በበኩሉ "ከሞያ ባልደረባነት አልፎ የልብ ወዳጅ ወንድሜ ማዲንጎ አፈወርቅን በህልፈተ ሕይወት ማጣቴን ማመን እስኪያቅተኝ ድረስ ኃዘኑን መቋቋም ከብዶኛል ። የመልካምነትህን ዋጋ እግዚአብሔር አምላክ ነፍስህን በአፀደገነት ያኑራት !!!" ብሏል። ተወዳጁ አርቲስት ቴዎድሮስ ካሳሁን (ቴዲ አፍሮ) በበኩሉ ባስተላለፈው የኃዘን መግለጫ መልእክት "በዝነኛውና በተወዳጁ ወንድሜ አርቲስት ማዲንጎ አፈወርቅ ድንገተኛ ህልፈተ ሕይወት የተሰማኝን ኃዘን ስገልጽ እጅግ በተሰበረ ልብ ነው" ብሏል። ማዲንጎ ቅን ሰው ነበር ያለው አርቲስት ቴዎድሮስ ካሳሁን ድምጻዊውን "ባለ ዕጹብ ተሰጥዖ" ሲልም አሞካሽቶታል።

አብዛኞቹም በዚህ ሰሞን የነበራቸውን የመድረክ ሥራ ሰርዘዋል። ሐሙስ መስከረም 19 ቀን 2015 ዓም የማዲንጎ ሥርዓተ ቀብር የተፈጸመበት እለት ነበር። በዚህ ዕለትም የታላቁ አርቲስት አስከሬን ከሙያ አባቱ ጥላሁን ገሰሰ አጠገብ አርፏል። በቀብሩ ሥነ ሥርዓት ላይ የኢፌዴሪ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር እና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ደመቀ መኮንን እና የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ አቡነ ማትያስን ጨምሮ በርካታ ታላላቅ ሰዎች እና በብዙ ሺ የሚቆጠር ሕዝብ በቦታው ተገኝቶ ነበር። በቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ከተደረገው ሥርዓተ ቀብር ቀደም ብሎ በወዳጅነት አደባባይ በተደረገው የሽኝት መርሐ ግብር ላይ ብዙዎች ስለ አርቲስቱ ያላቸውን ስሜት አጋርተዋል።

ከነዚህም መሀከል ልጁ ዲቦራ ማዲንጎ አንዷ ናት። "ማዲንጎ ልዩ አፍቃሪና ትሁት ሰው ነበር። እናንተ የምታውቁት እንደ አርቲስት ነው። የኔ ግን አባቢ ነው። ደስታ የሚሰማኝ በአጭር ጊዜ ሀገር የሚያኮራ ሥራ በመሥራቱ ነው" በማለት በሞቱ ብታዝንም በሥራው እንደምትኮራ ገልጻለች። አንጋፋው ድምፃዊ መሐሙድ አሕመድ "ዛሬ ልጄን አጥቻለሁ፤ አይዞህ ባይ ደጋፊዬን ምን ጎደለህ ባዬን አጥቻለሁ" በማለት የኃዘኑን ጥልቀት ተናግሯል። የመከላከያ ሚኒስቴር የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊው ኮሎኔል ጌትነት አዳነ "ማዲንጎ ከመጣና ከሄደ ሥርዓት ጋር ሳይሆን ከሀገር ወዳድ ጀግኖች ጋር መሆኑን ለሠራዊቱ ግንባር ዘልቆ ፍቅር አሳይቷል። ሀገር መውደድ ማለትም ደመራው ወዴት ይወድቃል ብሎ የሚደረግ ሳይሆን እንደዚህ በጽናት የሚደረግ መሆኑን አሳይቷል" ብለዋል።

የባህልና ስፖርት ሚኒስትሩ አቶ ቀጀላ መርዳሳ በበኩላቸው "ሞት የተፈጥሮ ሕግ ቢሆንም እንደ ማዲንጎ ያሉ የሀገር ተቆርቋሪዎች ሲያልፉ ያሳዝናል። ድምጻዊው በሁሉም ማኅበረሰብ ዝና እና ተቀባይነት ያለው ነው። ሁለት ዓይነት ሞት አለ፤ ተራ ሞትና እንደ ማዲንጎ ያለ የጀግና ሞት። በወያኔ ምክንያት አንዳንዶች በልባቸው ተሸነፍን ሲሉ እሱ ግን በልበ ሙሉነት ደፍሮ ሀገሩን ለማገልገል ወደ ግንባር ዘምቷል" በማለት ጀግንነቱን አስታውሰዋል። የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ አዳነች አቤቤ በበኩላቸው "ድምፃዊ ማዲንጎ አፈወርቅን በቅርብ አውቀዋለሁ። ሀገሩን የሚወድና እራሱን ለሀገሩ የሰጠ መልካም አርቲስት ነበር። ሀገራችን ጭንቅ ሲገጥማት ራሱን የሰጠ ሰው ነው። በሥጋ ቢያልፍም ዘመን ተሻጋሪ ሥራዎችን ትቶ ነው ያለፈው" ሲሉ ገልጸዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ባህል ፤ ኪነ ጥበብ እና ቱሪዝም ቢሮ ምክትል ኃላፊውና የሙዚቃ ሀያሲው አቶ ሠርጸ ፍሬስብሐት "ድምጻዊው ዜማን ዜማ እስከማይመስል ድረስ ከራሱ ጋር አዋህዶ የሚቀልጽ ሰው ነበር፤ አርቲስቱ በአጭር ጊዜ ዘመን አይሽሬ ሥራዎችን በመሥራት የሁላችንም ምሳሌ የሆነ ሰው ነው" በማለት የማዲንጎን የሙዚቃ አቅም ዘክረዋል።

# ስፖርት





## በእንቅፋቶች ያልተበገረችው ፈጣን የማራቶን አትሌት

**ቦጋለ አበበ**

ባለፈው ሳምንት በተካሄደው በርሊን ማራቶን በሴቶች አሸናፊ የሆነችው ኢትዮጵያዊቷ አትሌት ትእግስት አሰፋ ውድድሩን ያጠናቀቀችበት 2:15.37 ሰዓት የኢትዮጵያ ክብረወሰን የዓለማችንም ሦስተኛዋ የማራቶን ፈጣን አትሌት አድርጓታል። ይህች በማራቶን ውድድሮች ትልቅ ስምና ልምድ የሌላት አትሌት ያስመዘገበችው ፈጣን ሰዓት ብዙዎችን ያነጋገረና ትእግስት አሰፋ ማን ናት? ብለው እንዲጠይቁ ያደረገ ነው። የዛሬው የስፖርት ማህደር አምዳችንም በዚህችው አስደናቂ አትሌት የአትሌቲክስ ሕይወት ላይ ያተኮረ ነው።

ሙሉ ስሟ ትእግስት አሰፋ ተሰማ ይባላል። የተወለደችው እኤአ በ1994 መጋቢት ወር ላይ ነው። አሁን ላይ የኢትዮጵያን የማራቶን ክብረወሰን ጨብጣ የርቀቱ የዓለማችን ሦስተኛዋ ፈጣን አትሌት ለመሆን የበቃችው ትእግስት የአትሌቲክስ ሕይወትን የጀመረችው በሆለታ በአንደኛ ደረጃ ት/ቤት በ100ና በ200 ሜትር ሩጫ ነው። በ2001 ዓም የኢትዮጵያ ሻምፒዮና በ200፣400 ሜትርና በ400 ሜትር ዱላ ቅብብል ወርቅ አጥልቃለች። በወቅቱ በነበራት ውጤት ክለቦች ቢፈልጓትም እንቢ በማለት ወደ ሆለታ ተመለሰች። በ2003 ኢትዮጵያ ሻምፒዮና በድጋሚ በማሸነፍ የኦሮሚያ ፖሊስ አትሌቲክስ ክለብን ተቀላቀለች። እኤአ 2012 በሱዳን የምስራቅ አፍሪካ ውድድር በ400 ሜትር ሁለተኛ ሆና አጠናቃለች። 2012 በአፍሪካ ሻምፒዮና ቤኒን ላይ በተመሳሳይ ርቀቶች ጥሩ ተፎካካሪም ነበረች።

እኤአ በ2013 በአፍሪካ ወጣቶች አትሌቲክስ ቻምፒዮና በ8 መቶ ሜትር የነሐስ ሜዳሊያ ያጠለቀችው ትእግስት፣ ከዓመት በኋላ ሞሮኮ ማራኬሽ በተካሄደው በአዋቂዎቹ የአፍሪካ አትሌቲክስ ሻምፒዮና ኢትዮጵያን ወክላ በመወዳደር 4ኛ ደረጃን ይዛ ነበር ያጠናቀቀችው። የ28 ዓመቷ ድንቅ አትሌት ባለፈው ሳምንት በማራቶን ታላቅ ስኬት ካስመዘገበችባት በርሊን ከተማ ጋር የተዋወቀችው ከ8 ዓመት በፊት ነበር። ይህም በአፍሪካ አትሌቲክስ ሻምፒዮና 4ኛ ሆና ባጠናቀቀችበት ተመሳሳይ ወር በርሊን ላይ በ8 መቶ ሜትር ያሸነፈችበት አጋጣሚ ነበር።

እኤአ በ2016 የፖርትላንድ ኦሪገን የዓለም የቤት ውስጥ አትሌቲክስ ሻምፒዮና ላይ በ8 መቶ ሜትር ሀገሯን ወክላ ተወዳድራለች። ይሁን እንጂ ከመጀመሪያው ዙር የማጣሪያ ውድድር ማለፍ አልቻለችም። በተመሳሳይ ዓመት በሪዮ ኦሊምፒክ በርቀቱ ኢትዮጵያን ወክላ ለመወዳደር ብትበቃም ከመጀመሪያው ዙር ማጣሪያ ማለፍ አልቻለችም። ይሁን እንጂ በማጣሪያው የውድድር ዓመቱ የራሷን ፈጣን ሰዓት በ2:00:21 አስመዝግባለች።

ትእግስት ከሪዮ ኦሊምፒክ በኋላ በትልልቅ ውድድሮች አልታየችም። ምክንያቱ ደግሞ እኤአ ከ2014 ጀምሮ የእግር ሕመም በተለይም የተረከዝ ጅማት ሕመም አጋጠማት እስከ ሪዮ ኦሊምፒክ ከሕመም ጋር በመታገል ነበር ስትወዳደር የቆየችው። በወቅቱ ሐኪሞችም ‹‹ከአሁን በኋላ የትራክ ሩጫ በስፓይክ ጫማ መሮጥ አትችይም›› እንደተባለች ለኢትዮ ራነርስ ተናግራለች። የገጠማት ሕመም እየጠነከረ በመምጣቱም 2017 ሙሉ በሙሉ ከውድድር ርቃለች። በ2018 መጨረሻ ወር አንድ ውድድር ብቻ በ10 ኪሎ ሜትር ሮጣም ሁለተኛ ነበር ያጠናቀቀችው።

በ2019 ሦስት ውድድር አድርጋ በዓመቱ መጨረሻ በቫሌንሺያ ግማሽ ማራቶን ሕመሙ እየተሰማት 68:24 ሮጣ ውድድሩን እንደጨረሰች ሕመሙ በከባድ ነበረና በሸክም ወጣች። እዛው ስፔን ወደ ሕክምና በተወሰደችበት ወቅት ነበር ሐኪሞች ሩጫን ትታ ሌላ የሥራ ዘርፍ ላይ እንድትሠማራ ምክር የለገሳት። በሌሎች የአውሮፓ አገራትም ባደረገችው ሕክምና ተመሳሳይ ምክር ነበር የተሰጣት። በሰላም ለውድድር ከቤት የወጣችው አትሌት




**የዓለማችን ሦስተኛዋ የማራቶን ፈጣን አትሌት ትዕግስት አሰፋ በበርሊን ማራቶን ያልተጠበቀ ታሪክ ሠርታለች፣**

በሁለት ክራንች ወደ ሀገሯ ለመመለስ ተገደደች።

‹‹ዳግም እችላለሁ እሮጣለሁ›› በማለት በእምነት በፅናት የቆመችው አትሌት ከወራት በኋላ እያገገመች መጣች። 2021 አጋማሽ በኋላም ክራንቿን ጥላ ወደ ልምምድ ለመመለስ በቃች። 3 የ10 ኪሎ ሜትር ውድድርም አድርጋ ሶስቱንም አሸነፈች። በሁለት ግማሽ ማራቶን ውድድሮችም ድል ቀናት።

ዛሬ ላይ በማራቶን ገናና ስም ያተረፈችበትን የማራቶን ውድድር ግን መሮጥ የጀመረችው ባለፈው መጋቢት ነበር። በሳውዲ ዓረቢያ መዲና ሪያድ ማራቶን ከወራት በፊት ለመጀመሪያ ጊዜ የአርባ ሁለት ኪሎ ሜትር ውድድሯን ያደረገችው ትእግስት በ2:34:01 ሰዓት ሰባተኛ ደረጃን ይዛ ነበር ያጠናቀቀችው።

ከግማሽ ማራቶን የመጀመሪያ ድሏ በኋላ ድምጿን አጥፍታ ባለፉት ጥቂት ወራት ጠንካራ ዝግጅት ስታደርግ የቆየችው ይህች ድንቅ አትሌት በበርሊን ማራቶን ሦስተኛውን የዓለም ፈጣን ሰዓት አስመዝግባ ታሸንፋለች ብሎ የጠበቀ አልነበረም። በተለይም የበርሊን ማራቶን በርቀቱ ገና ሁለተኛ ውድድሯ እንደመሆኑ ካላት ትንሽ ልምድና በመጀመሪያ ውድድሯ ካስመዘገበችው ደካማ ሰዓት አኳያ እንኳን ፈጣን ሰዓት ለማስመዝገብ ለጠንካራ ተፎካካሪነትም ያጫት አልነበረም።

በዓለም ታላላቅ ከሚባሉ የማራቶን ውድድሮች አንዱና ዋነኛው በሆነው የበርሊን ማራቶን በወንዶች በርካታ የዓለም ክብረወሰኖች ቢሰበሩም በሴቶች ረገድ ያለው ታሪክ ተቃራኒ ነው። ማንም ያልጠበቃት ኢትዮጵያዊት አትሌት ግን 2:15:37 ሰዓት በማጠናቀቅ በአንድ ውድድር ሦስት የተለያዩ ክብረወሰኖችን መጨበጥ ቻለች። አንዱ የውድድሩን ክብረወሰን ከሁለት ደቂቃ በላይ ያሻሻለችበት ሲሆን ሌላኛው የኢትዮጵያ የማራቶን ክብረወሰን የጨበጠችበት ነው፣ ቀሪው ደግሞ በታሪክ ሦስተኛውን ፈጣን ሰዓት ያስመዘገበችበት ነው።

ትእግስት በዚህ ውድድር ቀድሞ በማራቶን ካስመዘገበችው ሰዓት ከሃያ ደቂቃ ያላነሰ መሻሻል ማሳየቷ ለማመን የሚከብድ ነው። ይህም በማራቶን ታሪክ ከኬንያዊቷ ብሪጊድ ኮስጌና ከእንግሊዛዊቷ ፓውላ ራድክሊፍ ቀጥላ ስሟ እንዲጠራ አድርጓታል። ከዚህች ኢትዮጵያዊት አትሌት የተሻለ የማራቶን ፈጣን ሰዓት ያስመዘገቡት ኮስጌ በ2019 የቺካጎ ማራቶን 2፡14፡14 ሲሆን የራድክሊፍ 2፡15፡25 የተመዘገበው እኤአ በ2003 ለንደን ማራቶን ላይ ነበር።




## ልጆች ስለኦቲዝም ምን ያህል ያውቃሉ?

**ጽጌረዳ ጫንያለው**

ልጆች እንዴት ናችሁ፤ ትምህርት እንዴት ይዟችኋል? በደንብ እያነበባችሁ ነው አይደል? ከመጀመሪያው ጀምሮ ማንበብን ልምምድ ካላደረጋችሁ ውጤታማ አትሆኑም። ስለዚህም ጎበዝ ተማሪ ለመሆን ከፈለጋችሁ ዛሬ የተማራችሁትን ዛሬውኑ በማንበብና ተጨማሪ ነገሮችን በማከል አቅማችሁን ማጎልበት አለባችሁ። ልጆች ዛሬ ይዤላችሁ የመጣሁት ከእስከዛሬው ለየት ያለ ጉዳይ ነው። ምን መሰላችሁ ስለ ኦቲዝም ተጠቂ ልጆችና ሥራዎቻቸው ነው። ስለዚህም ኦቲዝምና ሌሎች ተያያዥ ችግሮች ስላሉባቸው ሕፃናት እንነጋገራለን።

ልጆች በደንብ እንድታውቁ እነግራችኋለሁ። መጀመሪያ ግን ስለ በሽታው ምንነት እንነጋገር። ኦቲዝም ምንድን ነው? ከሚል ብንነሳ ኦቲዝም የአዕምሮን እድገት ውስንነት እንደሆነ ምሑራን ያስረዳሉ። ከአዕምሮ እድገት ጋር በተያያዘ ነገሮችን ቶሎ መረዳት አለመቻል በስፋት በተጠቂዎቹ ዘንድ ይታያል። ይህ ደግሞ አካላዊ ጤናን ጭምር ሊያቃውስ ይችላል።

ሁሉም ኦቲዝም ያለባቸው ሰዎች ይነስም ይብዛም ብዙ የሚያመሳስላቸው ነገሮች አሉ። ለአብነት ከሚታዩ ችግሮች መካከል፡- ውስን የሆነ ስሜታዊነት አንዱ ነው። ማለትም የራሳቸውን ማንነት መግለጽም ይሁን ሌሎችን መረዳት ይከብዳቸዋል። በማንኛውም አፍ መፍቻ ቋንቋ መግባባት ይቸግራቸዋል። ማኅበራዊ ግንኙነት ላይም ይቸገራሉ። ማለትም የራሳቸውን እንጂ የሌሎችን ሰዎች ስሜት መረዳት ቀላል አይሆንላቸውም።

ሌላው የሚደጋገም ባህሪያት/የተለመዱ ነገሮችንን መውደድ፤ ለነገሮች ባልተለመደ መልኩ ስሜታዊ መሆን ይታይባቸዋል። አንድ ነገር ላይ ከመጠን በላይ ማተኮር ይፈልጋሉ። ተደጋጋሚ የሆነ ትርጉም የማይሰጥም ሆነ የማይገባ ቃላት ወይም ድምጽ ወይም እንቅስቃሴ ሊያሳዩ ይችላሉ። ስለዚህም ለእነዚህ ልጆች ጥብቅ ክትትል




ማድረግ ይገባችኋል።

ኦቲዝም በማኅበራዊ ግንኙነት ላይ፣ በተግባቦት ላይ ከሚያደርሰው ተፅዕኖ አንፃር ሦስት አይነት ደረጃዎች አሉት። የመጀመሪያው መጠነኛ የሆነ የሌላ ሰው ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው የኦቲዝም ተጠቂ ልጆች ናቸው። ሁለተኛው ደግሞ ከሰዎች ጋር ለመግባባት፣ ራሳቸውን ለመጠበቅ ከፍተኛ የሆነ የሌላ ሰው ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ሲሆኑ፤ በሦስተኛ ደረጃ የምናነሳው ደግሞ መጠነኛ የሆኑ ነገሮች ለማድረግ በጣም ከፍተኛ የሆነ የሌላ ሰው ድጋፍ የሚጠይቁት ናቸው። ስለሆነም እነዚህን ማገዝ ከእድሜ እኩዮቻቸው የሚጀምር ነውና እናንተ በድጋፍ ማገዝ ይኖርባችኋል። ምን እናድርግ ካላችሁ የሚከተሉትን ብታደርጉላቸው በቂ ነው።

ለኦቲዝም ተጠቂዎች የሚሰጠው ሕክምና ዓላማው የኦቲዝም ምልክቶችን በመቀነስ ያላቸውን ችሎታ በመደገፍ ልጆች ቢያንስ ራሳቸውን ችለው እንዲንቀሳቀሱ ማስቻል ነውና ለቤተሰብ በመንገር እንዲመረመሩና ክትትል እንዲደረግላቸው ማድረግ ነው። እናንተም ብትሆኑ ልጆቹ በማኅበራዊ ግንኙነታቸዉ የተለዩ እንዲሆኑ ቀርባችሁ የሚፈልጉትን ማድረግ አንዱ እገዛ ነው።

በሌላ በኩል ማድረግ ያለባችሁ ነገር በሁኔታዎች ወይም በአካባቢያቸው በሚፈጠሩ ተግባራት እንዳይደናገጡ ማገዝ ነው። ለዚህ ደግሞ ተደጋጋሚ መልካም ልምምዶችን እንዲያደርጉ መደገፍ አለባችሁ። በአስጨናቂ እና በማያውቋቸው ሁኔታዎች እና አካባቢዎች ተጨማሪ ድጋፎችን ይፈልጋሉና ይህንንም ልታደርጉላቸው ይገባል።

ሌላው ማድረግ ያለባችሁ ቃላቶችን ማውጣት ባይችሉም ሌሎች መንገዶችን በመጠቀም መግባባትንና መማር ይችላሉና ይህንን እያየችሁ ማበረታታት ነው። እነርሱን ለመደገፍ ካሰባችሁ ነገሮችን በተደጋጋሚ እንዲሞክሯቸው እድሎችን መስጠትም አለባችሁ።

ልጆች ለመሆኑ ኦቲዝም ያለባቸው ልጆች የተወሰነ የሥራ ዘርፍ ላይ የአዕምሮ አቅማቸው ከፍተኛ እንደሆነ ታውቃላችሁ? ለምሳሌ፡- በሙዚቃ፣ በሒሳብ፣ በቴክኖሎጂ ፣ በስነ-ጥበብ እና በምሕንድስና መስኮች ውስጥ አብዛኞቹ የተዋጣላቸው ሥራ ይሠራሉ። ከማኅበረሰቡም ሐቀኞች ናቸው፣ ማጭበርበር፣ ማስመሰል ወይም መዋሸት አይፈልጉም፣ ምን ያመጣብኛል የሚለውን አይጨነቁበትም። ለማንኛው ከዚህ ጋር በተያያዘ አንድ ነገር ልንገራችሁ። ሀገር አቀፍ የልዩ ፍላጎት (አካቶ ትምህርት) ጉባኤ በተካሄደበት ወቅት ሥራቸውን ለታዳሚዎች ያቀረቡ የኦቲዝም ተጠቂ ልጆች ነበሩ።

ልጆቹ በሁሉም ቋንቋ የመጨፈር ብቃታቸው እጅግ የሚያስደንቅ ነው። ዘፈኑን ጭምር ሸምድደውታል። እንቅስቃሴያቸው ደግሞ በእኩል ደረጃ የሚከወን ነበር። ይህ የሚያሳየው ደግሞ ተደጋጋሚ ልምምድ ካደረጉ ብቃታቸውን ማስመስከር እንደሚችሉ ነው።

ልጆች ከላይ እንዳልኳችሁ የኦቲዝም ተጠቂ ልጆች በእጅ ሥራውም የተለየ ክህሎት ያላቸው ናቸው። ለዚህ ምስክር የሚሆነንም እነዚሁ ልጆች ያቀረቧቸው ነገሮች ናቸው። የአልጋ መውረጃ ምንጣፍ፣ ዳንቴል፣ የስኒ ልብስና የመሳሰሉትን ሠርተው ለታዳሚው ሲያሳዩ ነበር። ይህ ደግሞ የሚያሳየን ድጋፍና ክትትል ከተደረገላቸው የራሳቸውን ገቢ በራሳቸው መፍጠር እንደሚችሉ ነው። ስለሆነም እናንተ በአቅራቢያችሁ አሉና በሁሉም ነገር ማገዝ ይኖርባችኋል። በተለይም ከላይ የጠቀስኩላችሁን ነገር ካደረጋችሁላቸው ስኬታማ እንዲሆኑ ትረዷቸዋላችሁ። ስለዚህ ልጆች የኦቲዝም ተጠቂ የሆኑትን ወንድምና እህቶቻችሁን አግዟቸው እሺ። ጎበዞች። ለዛሬ ሀሳባችንን በዚህ እንቋጭ። በቀጣይ በሌላ ጉዳይ እስክንገናኝ ቸር ሰንብቱ!!